# አዲስ ዘመን

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 087 ኅዳር 27 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ባህላዊ የአጥንት ሕክምናና መዘዙ

አስናቀ ፀጋዬ

**ዜና ሐተታ**

በኢትዮጵያ ከባህላዊ የአጥንት ህክምና/ ወጌሻ /ጋር ተያይዞ የጎንዮሽ ጤና ጉዳቶች እየጨመሩ መምጣቸውን /Bone Setting Associated Disability/ የተሰኘው ሀገር አቀፍ የጥናት ቡድን በቅርቡ ያካሄደው ጥናት አመላከቷል። ለመጨመሩ ምክንያቱ ምንድን ነው፣ መፍትሄውና ጉዳቱስ ምን ይመስላል ስንል ምሁራንን አነጋግረናል፡፡

የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ዶክተር መንግስቱ ገብረዮሐንስ በሙያቸው የአጥንትና መገጣጠሚያ ስፔሺያሊስትና የጀርባ አከርካሪ ሰብ ስፔሺያሊስት ሀኪም ናቸው። ሀገር አቀፍ የጥናት ቡድኑን ከመሰረቱት ውስጥም አንዱ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ደግሞ የኢትዮጵያ አጥንትና መገጣጠሚያ ሀኪሞች ማህበር ፀሀፊም ሆነው እየሰሩ ነው፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ በጥናቱ ከሶስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ከጤና ተቋማት የመጡ፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉና በባህላዊ መንገድ ታክመው የአጥንትና መገጣጠሚያ ጉዳት የደረሰባቸው አካላት ተካተው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ለጥናቱ በተሰበሰበው መረጃ

ባህላዊ የአጥንት... ወደ ገጽ 3 ዞሯል



# በክንፎቹ ከፍታውን በብቃቱ ሽልማቶችን የተቆጣጠረው - አየር መንገድ

አስቴር ኤልያስ

**ዜና ትንታኔ**

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የእ.ኤ.አ 2024 ምርጡ የአፍሪካ አየር መንገድ መሆኑን በዓለም አቀፍ ደረጃ አየር መንገዶችን የሚገመግመው ስካይትራክስ ድርጅት በድረ ገጹ አሳውቋል፡፡ ይህንንም ሽልማት ለተከታታይ ሰባት ዓመታት ማግኘቱን አመልክቷል። በዚሁ ዓመት አየር መንገዱ የአፍሪካ ምርጥ ቢዝነስ ክላስና ኢኮኖሚክ ክላስ እንዲሁም በአፍሪካ ለኢኮኖሚ ክላስ ተጓዦች ምርጥ የበረራ ላይ ምግብና መጠጥ አቅራቢነት በጥቅሉ አራት ሽልማቶችን አግኝቷል።

የአየር መንገዱ ለተከታታይ ዓመታት የከፍታ ማማውን አስጠብቆ የቀጠለውና ብዙ ሽልማቶችን ያገኘበት ምስጢር ምንድነው? አየር መንገዱ ስኬታማ መሆን ለሀገር ያለው ፋይዳ ምን ያህል ነው? ስንል የተለያዩ ምሁራንን አነጋግረናል፡፡

በኢትዮጵያ አየር መንገድ አማካይነት ኢትዮጵያ የምታገኛቸው ሽልማቶች ትልቅ አቅም የሚፈጥሩ ከመሆናቸውም ባሻገር እንደ ሀገር ታላቅ ኩራትም የሚሉት

በክንፎቹ ከፍታውን... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



# ‹‹መሪነት ሀገርን ከድህነት ወደ ብልፅግና የማሻገር የትውልድ አደራ ነው››

- አቶ ተመስገን ጥሩነህ
ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር

ኢያሱ መሰለ

አዲስ አበባ፡- መሪነት ለትውልድ መሥራት ነው፤ ሀገርን ከድህነት ወደ ብልፅግና የማሻገር ርዕይ ያነገበ የትውልድ አደራም ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ገለጹ፡፡

" መሪነት ሀገርን... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የጥጥ ኮንትራት እርሻን ለማስፋፋት ትኩረት ተሰጥቷል

ማህሌት አብዱል

አዲስ አበባ፡- የጥጥ ልማቱንና ኢንዱስትሪው በዘላቂነት በቀጥታ ተሳስረውና ተናበው እንዲሄዱ የጥጥ ኮንትራት እርሻ ለማስፋት ርብርብ እያደረገ እንደሚገኝ ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የጥጥ ልማት ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሳምሶን አሰፋ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያ ለጥጥ ልማት ምቹና ተስማሚ አግሮ ኢኮሎጂ ካላቸው ሀገራት መካከል አንዷ ነች፡፡ በተለይም ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ሶማሌ፣ አፋር ክልሎች፣ የአማራ ክልል ምእራብ ጎንደርና የመሳሰሉት አካባቢዎች እንዲሁም ኦሮሚያ ላይ ከፍተኛ ጥጥ ማምረት የሚያስችል አቅም አላት፡፡

በኢትዮጵያ የአሠራር ሥርዓቶችን በማዘመን የጥጥ ኮንትራት እርሻን ለማስፋፋት በልዩ ትኩረት እየተሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ የጥጥ ልማቱን ከኢንዱስትሪው ጋር በቀጥታ በማስተሳሰር ከልማቱ የበለጠ ለመጠቀም በቅንጅት እየተሰራ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ጥናቶችም ሀገሪቱ ጥጥ በዝናብም በመስኖም ሊለማባት የሚያስችል ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንዳላት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እስካሁን ማልማት የተቻለው ግን ከ100 ሺ ሄክታር አይበልጥም ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፡፡



ከአነስተኛ እስከ ሰፋፊ እርሻዎች በጥጥ ልማት በቀጥታና በተዘዋዋሪ በየዓመቱ እስከ ሁለት ሺህ የሚደርሱ አልሚዎች እንደሚሳተፉ ጠቅሰው፣ በየዓመቱ ከ30 ሺህ እስከ 50 ሺህ የሚደርሱ አነስተኛ ማሳ ያላቸው አርሶ አደሮች በጥጥ ልማት እንደሚተዳደሩ ጠቁመዋል፡፡ ካለው እምቅ አቅም አኳያ በዘርፉ ተጠቃሚ የሆነው ዜጋ ቁጥር አነስተኛ የሚባል እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡

በአንፃሩ እንደ ቻይና፣ ብራዚልና አሜሪካ ያሉ ሀገራት ከጥጥ ልማት ከአምስት ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ እንደሚያገኙ ጠቅሰው፤ እነዚህ ሀገራት ከ30 እስከ 50 ሚሊዮን ዜጎቻቸው የሥራ እድል ተጠቃሚ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

የጥጥ ኮንትራት... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል 146 ሺህ 686 ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ለማልማት ታቅዷል

## - 4 ሺህ 449 ሄክታሩ በበጋ መስኖ ስንዴ የሚሸፈን ነው

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በ2017 የበጋ መስኖ ልማት 146 ሺህ 686 ሄክታር መሬት በማልማት 35 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ማቀዱን የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡ ከዚህ ውስጥ አራት ሺህ 449 ሄክታር መሬቱ በበጋ መስኖ ስንዴ የሚሸፈን መሆኑንም ጠቁሟል፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊና የእርሻ ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ዓለምይርጋ ወልደሥላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በክልሉ በ2017 የበጋ መስኖ ልማት በሁለት ዙሮች በሆርቲካልቸርና በአዝዕርት ሰብሎች 146 ሺህ 686 ሄክታር መሬት በማልማት 35 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡ ፡ ከዚህ ውስጥም አራት ሺህ 449 ሄክታር መሬቱ በበጋ መስኖ ስንዴ የሚሸፈን ነው ብለዋል፡፡

አቅዱን ለማሳካት በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ እንዲሁም በቀበሌ ደረጃ የንቅናቄ መድረኮችን በማካሄድ አቅዱን የጋራ የማድረግ እና የመግባባት ሥራ ተሠርቶ



አቶ ዓለምይርጋ ወልደሥላሴ

ወደ ትግበራ ተገብቷል ያሉት አቶ ዓለምይርጋ፣ ከዚህ ጎን ለጎንም የውሃ አማራጮችን የመለየት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በዚህም በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች ላይ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ተጀምሯል ነው ያሉት፡፡

እስካሁን ድረስ 68 ሺህ 311 ሄክታር መሬት መታረሱን ጠቅሰው፣ ከዚህ ውስጥ 49 ሺህ 521 ሄክታር መሬትም ማልማት ተችሏል ብለዋል፡፡

ለበጋ መስኖ ልማት አርሶ አደሩ ከመኸር እርሻ የተረፈውን ግብዓት እየተጠቀመ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን የተገኘውን 10 ሺህ ኩንታል በላይ ማዳበሪያ መስኖ ቀድመው ለሚዘሩ አርሶ አደሮች እንዲደርስ መደረጉንም ጠቁመዋል፡፡

በተወሰነ መልኩ እጥረቶች ቢኖሩም ተጨማሪ ግብዓት ለማቅረብም እንደሀገር ርብርብ እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የግብርና ሥራ የሁሉንም ባለድርሻዎች ተባብሮ መሥራት የሚጠይቅ መሆኑን ያስታወሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፣ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ሁሉም ሥራዎች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲከናወኑ ማድረግ ይጠይቃል፡፡ ለዚህም በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ ባለሙያዎችና አርሶ አደሮች የየድርሻቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ አቶ ዓለምይርጋ ወልደሥላሴ ጠይቀዋል፡፡

# የሀገሪቱ የዲጂታል ልማት ወደ አስተማማኝ ደረጃ እያደገ ነው

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- የሀገሪቱ የዲጂታል ልማት ወደ አስተማማኝ ደረጃ እያደገ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) 2ኛው ሀገራዊ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ ትናንት በአዲስ አበባ ሲከፈት እንደገለጹት፣ በዲጂታል መታወቂያ እና የዲጂታል ክፍያዎች ለማስፋፋት በመንግሥትም ሆነ በግሉ ዘርፍ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች የሀገሪቱ የዲጂታል ልማት ወደ አስተማማኝ ደረጃ እያደገ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

እነዚህ የልማት ሂደቶች የኢትዮጵያን ዲጂታል ራዕይ ለመደገፍ እና ዘላቂ እና የማይበገር የዲጂታል መሠረተ ልማት እድገትን ለማረጋገጥ መሰረት የሚጥሉ መሆናቸውን አስገንዝበዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ባለፉት አራት ዓመታት በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ እና በዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ማሕቀፎች የዲጂታል ልማቱን ለማሳካት በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን ጠቁመው፣ በወሳኝ መሰረተ ልማቶች ዝርጋታ እንዲሁም በርቀት የሚገኙ አካባቢዎችን በማስተሳሰር እና በተለያዩ የኃይል አማራጮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህም በተጨማሪ የዲጂታል ዘርፉ ሁሉን አሳታፊ፣ ጤነኛ እና ዘላቂ እድገት እንዲኖረው የሚያስችሉ በርካታ የህግ ማሕቀፎች ወጥተው ስራ ላይ እንዲውሉ መደረጉን ተናግረዋል።

የግሉ ዘርፍም የዳታ ማዕከላትን በማስፋፋት እና አዳዲስ የዲጂታል አገልግሎቶችን በማቅረብ እያደረገ ያለው ተነሳሽነት ለዲጂታል ኢትዮጵያ ስኬት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

መንግሥት የጀመረውን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ አጠናክሮ በማስቀጠል የዲጂታል እድገቱን አሳታፊ እና አካታች ለማድረግ ቁርጠኛ ነው ብለዋል። ስንተባበር ለወደፊቷ ዲጂታል ኢትዮጵያ አዳዲስ እድሎችን መፍጠር እና ችግሮችን መፍታት እንችላለን ያሉት ዶክተር በለጠ፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የዳበረ ዲጂታል ስነ-ምህዳር ለመፍጠር ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር የሚያደርገውን ትብብር አጠናክሮ እንደሚያስቀጥል አመላክተዋል።

አካታች ዲጂታል ኢኮኖሚን ለማረጋገጥ የዲጂታል እውቀት ያለውን ወሳኝ ድርሻ በመረዳት መንግሥት በተለይ የአምስት ሚሊዮን ኮደሮች ፕሮግራም በመንደፍ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

በሌላ በኩል የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ መካሄድ ፖሊሲዎችን ለማጠናከር፣ የአቅም ግንባታ ውጥኖችን ለማሳካት እና የባለብዙ ባለድርሻ አካላት ትብብርን ለማጎልበት እንደሚረዳ ገልጸዋል፡፡

በይነ መረብ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ ያለው ሚና እየጨመረ መጥቷል ያሉት ሚኒስትሩ፣ የበይነ መረብ አስተዳደር፣ ተጠያቂነት እና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለሀገር እድገት ወሳኝ ናቸው ነው ያሉት፡፡

ኢትዮጵያ ለምታደርገው የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ አስተማማኝ እና አካታች የበይነ መረብ አስተዳደር ወሳኝ መሆኑን እንገነዘባለን ሲሉ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

# የቆዳውን ዘርፍ ተግዳሮቶች በመፍታት ምርትና ጥራትን ለማሳደግ እየተሠራ ነው

## . ለውጭ ገበያ ከቀረቡ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ስምንት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ዶላር ተገኘ

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- የቆዳውን ዘርፍ ተግዳሮቶች በመፍታት የቆዳ ምርትና እና ጥራትን ለማሳደግ እየተሰራ መሆኑን የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል አስታወቀ። ባለፉት አራት ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረቡ የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ስምንት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር መገኘቱን ገለጸ፡፡

የማዕከሉ ስራ አስኪያጅ ተወካይ አቶ መሐመድ ሁሴን በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳስታወቁት፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የዘርፉን ማነቆዎች ለመፍታት በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ማዕከሉ በኩል በትኩረት እየሰራ ይገኛል። ማነቆዎቹን ለመፍታት በየፋብሪካዎቹ እና በየኩባንያዎቹ ደረጃ ያሉትን ችግሮች መሰረት አድርጎ ለመፍታት እየሰራ ነው፡፡ ለውጤታማነቱም የዘርፉ ባለድርሻዎች ቅንጅታዊ አሰራር ያስፈልጋል።

በኢንዱስትሪዎች ዘንድ የበሬ፣ የበግና የመሳሰሉት ቆዳዎች ፍላጎት እንዳለ ጠቅሰው፣ የቆዳ ሰብሳቢዎች ከገበያ መውጣት ችግር ይህን ፍላጎት መመለስ እንዳላስቻለ ተናግረዋል፡፡

በአቅራቢዎች እና ተቀባዮች መካከል ያለው ግብይት ግልፅነት የጎደለው መሆኑንም አመልክተው፣ በዘርፉ እሴት የማይጨምሩ ተዋናዮች መብራከትና የጨው ዋጋ መወደድ የቆዳ ዘርፉ ሌሎች ተግዳሮቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በቅርቡ ስራ ላይ የዋለው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ በአምራች ኢንዱስትሪው ሲጠየቅ የኖረ መሆኑን አስታውቀው፣ ተቀዛቅዞ የቆየውን የቆዳ ዘርፍ እንደሚያነቃቃ አስታውቀዋል። ማሻሻያው የቆዳና ሌጦ አምራች ፋብሪካዎች ኬሚካል ከውጭ ሲያስመጡ ለሚያስፈልጋቸው የውጭ ምንዛሪ ግኝት ጠቃሚ መሆኑን ገልጸዋል።

አሳቸው እንዳሉት፣ ማሻሻያው የውጭ ምንዛሬ አቅርቦቱን የሚያሻሽል በመሆኑና አምራቹ ወደ ውጭ በሚልካቸው ምርቶች ከሚያገኘው የውጭ ምንዛሬ 50 በመቶ በቀጥታ እንዲጠቀምበት፣ የተቀረውን 50 በመቶ ደግሞ በራሱ አካውንት አስቀምጦ በፈለገ ጊዜ እንዲጠቀምበት የሚያስችል አሰራር የተፈጠረበት



ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ከውጭ ለሚያስመጡት ግብአት እንዲያውሉት እንደሚያስችል ገልጸዋል፡፡

ቀደም ሲል ግብዓት ለማምጣት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ችግር እንደነበር አስታውሰው፣ የኬሚካል ግብዓት እጥረት ባለበት ሁኔታ ለማምረት አዳጋች እንደነበር አስታውቀዋል። ማሻሻያው የግብዓት አቅርቦቱን ችግር በከፍተኛ ሁኔታ የሚቀርፍ ይሆናል ነው ያሉት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሐምሌ ወር 2016 ጀምሮ እስከ ጥቅምት 2017 ዓ.ም ባሉት አራት ወራት ወደ ውጭ ከተላኩ የቆዳና የቆዳ ውጤት ስምንት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘቱንም ተወካዩ አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፣ ከዚህ ውስጥ ወደ አራት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የተገኘው የቆዳ ፋብሪካዎች ወደ ውጭ ከላኩት ምርት ነው። ዜሮ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላሩ ደግሞ የቆዳ ጓንት አምራቾች ከላኩት ምርት የተገኘ ነው። ዜሮ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር የቦርሳ፣ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር ደግሞ ከቆዳ ተረፈ ምርት እሴት በመጨመር በመላክ የተገኘ ነው።

ይህ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከሚጠበቀው በታች መሆኑን ጠቅሰው፣ በዘርፉ ያሉትን ተግዳሮቶች ለመፍታት እንዲሁም የቆዳ ምርቱን እና ጥራቱን ለማሳደግ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

አቶ መሀመድ የከፊልና ያለቀለት የቆዳ ውጤት የኢትዮጵያ የገበያ መዳረሻ በአብዛኛው ቻይና መሆኗን ጠቁመው፣ ወደ ቻይና የሚላከው ምርት በኮቪድ ምክንያት በከፍተኛ ሁኔታ መቀነሱን አስታውሰዋል። ወደ ቻይና የሚላከው ምርት አሁን ወደ ነበረበት የመመለስ አዝማሚያ እያሳየ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ምርቶችን ለአሜሪካ በመሸጥ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው ኩባንያዎች በውስጣዊ ምክንያት ማምረት አቁመው እንደነበር አስታውሰው፣ ከእነዚህ ኩባንያዎች መካከል ሁኣጂያን የጫማ ፋብሪካ አንዱ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ኩባንያው የቆዳ ውጤቶችን በከፍተኛ ደረጃ ወደ አሜሪካ ይልክ እንደነበረ አስታውሰው፣ እንደገና ወደ ማምረት ስራ መግባቱን ገልጸዋል፡፡ የናሙና ምርት ወደ አፍሪካ ሀገራትና ሌሎች ሀገራት መላክ መጀመሩንም አመላክተዋል።

ዜና



አምባሳደር ነብያት ጌታቸው

# የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው አዲስ መነቃቃት ፈጥሯል

## - በአዲስ አበባ የሚገኙ የውጭ ሀገራት ኤምባሲዎች ቁጥር ወደ 137 አድጓል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው አዲስ መነቃቃት መፍጠሩን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡ በአዲስ አበባ የሚገኙ የውጭ ሀገራት ኤምባሲዎች ቁጥር 137 ከፍ ማለቱም ተገልጿል፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር ነብያት ጌታቸው ትናንት ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው ሁሉን አቀፍ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው አዲስ መነቃቃት ፈጥሯል፡፡ ይህም ይበልጥ የኢንቨስትመንት ተጠቃሚ ለመሆን ሰፊ ዕድል ይፈጥራል፡፡

ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ከዘጠኝ ሀገራት በላይ የተውጣጡ በድምሩ ከ20 በላይ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ለመሠማራት ጉብኝት አድርገዋል ያሉት አምባሳደር ነብያት፤ በኢነርጂ መሠረተ-ልማት ፣ ግብርና፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ፣ የማዕድንና የቱሪዝም ዘርፎች ላይ ለመሰማራት ፍላጎት አላቸው ብለዋል፡፡

በኢንቨስትመንትና ምጣኔ ሀብት ረገድም አበረታች ተግባራት መከናወናቸውን ጠቅሰው፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያን ተከትሎ የተለያዩ ሀገራት ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ኢንቨስት የማድረግ ፍላጎት እያሳዩ መሆኑን ተናግረዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጌዲዮን ጢሞቴዎስ (ዶ/ር) ከፈረንሳይ እና የአውሮፓ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጂያን ኖኤል ባሮት ጋር ውይይት ማድረጋቸውን በመግለጽ፤ የኢትዮጵያና የፈረንሳይን አጋርነት ማጠናከር የሚያስችሉ በትምህርት፣ ኢንቨስትመንት፣ የኃይል አቅርቦትና ሌሎችም ጉዳዮች ላይ መወያየታቸውን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሟን ባስጠበቀ መልኩ ለቀጣናው ሰላምና ደኅንነት በትኩረት እየሰራች መሆኑን ገልጸው፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር አሊ የሱፍ አሕመድ አል-ሻሪፍ ጋር መወያየታቸውንም ተናግረዋል፡፡

ሚኒስትሩ ከእስያ መሠረተ-ልማት ኢንቨስትመንት ባንክ ፕሬዚዳንት ጂን ሊኩን ጋር በኢትዮጵያና በባንኩ መካከል ያለውን ትብብር ለማጠናከር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ መምከራቸውንም ገልጸዋል።

ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴ 24 የውጭ ሀገራት አዳዲስ አምባሳደሮች የሹመት ደብዳቤቸውን መቀበላቸውን የገለጹት አምባሳደር ነብያት፤ አምባሳደሮቹ ሀገሮቻቸው ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚሠሩ መግለጻቸውን ተናግረዋል። ኮሎምቢያ አዲስ ኤምባሲዋን በአዲስ አበባ ለመክፈት ዝግጅት እያደረገች መሆኑን በመግለጽ፤ አዲስ ኤምባሲዋን ለመክፈት የምትገኘው ኮሎምቢያ አምባሳደርም የሹመት ደብዳቤያቸውን እንዳቀረቡ ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ የሚገኙ የውጭ ሀገራት ኤምባሲዎች ቁጥር ወደ 137 ከፍ ማለቱን በመግለጽ፤ መዲናዋ የዲፕሎማሲ መዲናነቷና ተፈላጊነቷ እየጨመረ ለመምጣቱ ማረጋገጫ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ የሁለት ሀገራት ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮችና የ9 ሀገራት ከፍተኛ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለስልጣናት በኢትዮጵያ ጉብኝት ማድረጋቸውን ጠቅሰው፤ ጉብኝቶቹ ኢትዮጵያ በቀጣናው ያላት የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ተሰሚነት እየጨመረ መምጣቱን የሚያሳይ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

በመዲናዋ ለሚካሄደው የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ቅድመ ዝግጅት እየተካሄደ ነው ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ለጉባኤው ኮሚቴ ተቋቁሞ አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ እንደሚገኝ ነው የገለጹት። በዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲም ከማይናማርና በሊባኖስ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው ለመመለስ እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።

# የሪል ስቴት አልሚዎች ከእንግዲህ 80 በመቶ ያልተጠናቀቀ ቤት ማስተላለፍ አይችሉም

## - ምክር ቤቱ ሦስት ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ አጸደቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- በአዲሱ አዋጅ የሪል ስቴት አልሚ ድርጅቶች ያለደንበኛው ፍላጎትና ፈቃድ አጠቃላይ ግንባታው ቢያንስ 80 በመቶ ያልተጠናቀቀ ቤት ለደንበኞች ሊያስተላልፉ እንደማይችሉ የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ እሸቱ ተመስገን (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን ትናንት ባካሄደው 9ኛ መደበኛ ስብሰባው የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረቡትን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ሦስት ረቂቅ አዋጆችን አጽድቋል።

የከተማ መሠረተ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ እሸቱ ተመስገን (ዶ/ር)፤የሪል እስቴት ልማት እና የማይንቀሳቀስ ንብረት ግብይትና ግመታ ረቂቅ አዋጅን አስመልክቶ የተዘጋጀውን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብም ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡

የሪል እስቴት ልማቱ አቅርቦት እጅግ ወደኋላ የቀረና የሕዝቡን ፍላጎት የማያሟላ በመሆኑ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ግመታ ሥርዓቱ ዘመናዊና በመረጃ በተደገፈ መልኩ ተገማች ዋጋ እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ እና በማይንቀሳቀስ ንብረት ገበያው ግልጽነት መጓደሉ የኢኮኖሚ መዛባት እያስከተለና የመንግሥትን ጥቅም የሚያሳጣ እንዳይሆን ለማድረግ የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አዲሱ አዋጅ የሪል ስቴት አልሚ ድርጅት ያለደንበኛው ፍላጎትና ፈቃድ አጠቃላይ ግንባታው ቢያንስ 80 በመቶ ያልተጠናቀቀ ቤት ለደንበኞች ሊያስተላልፍ እንደማይችል አስቀምጧል ብለዋል።

በተጨማሪ በሪል ስቴት ልማት ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም አካል የውሸት ማስታወቂያ ማስነገር እንደማይችልም ደንግጓል፡፡

ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ረቂቅ አዋጁ፤ አዋጅ ቁጥር 1357/2017 ሆኖ በሁለት ተቃውሞና በአንድ ድምፀ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል፡፡

በተመሳሳይም እሸቱ ተመስገን (ዶ/ር) የኢትዮጵያ ሕንፃዎች ረቂቅ አዋጅን አስመልክቶ በቋሚ ኮሚቴው የተዘጋጀውን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡

በማብራሪያቸውም፤ ረቂቅ አዋጁ በነባሩ ሕግ በአፈፃፀም የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን የሚፈታ፣ የአካል ጉዳተኞችን ተደራሽነት የሚያረጋግጥ፣ የግንባታ ጥራትና የሀብት ብክነት ችግሮችን ይቀርፋል፡፡

በተጨማሪም ግልጽና ለአተገባበር ምቹ የሆነ የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት ያስችላል ብለዋል፡፡

ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ የኢትዮጵያ ሕንፃዎች አዋጅን፤ አዋጅ ቁጥር 1356/2017 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አፅድቆታል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ምክር ቤቱ በውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዲማ ነገዎ (ዶ/ር) የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ አዋጅ ቁጥር 1072/2010 ማሻሻያ አዋጅን ለማጽደቅ የቀረበውን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ አዳምጧል፡፡

ሰብሳቢው በማብራሪያቸው፤ የውሳኔ ሃሳብ ኤሌክትሮኒክ ፊርማ አዋጅ ቁጥር 1072/2010 ለመተግበር የሚያስፈልጉ ደንብና መመሪያዎችን አውጥቶ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ውክልና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አለመስጠቱ አዋጅ ቁጥር 1072/2010 ተፈፃሚ ለማድረግ ተቋሙ መቸገሩንና የተቋሙ ሥራ መጓተቱን ቋሚ ኮሚቴው ተገንዝቧል፡፡

በመሆኑም ቋሚ ኮሚቴው ረቂቅ አዋጁን ከመረመረ በኋላ አስፈላጊነቱን በሙሉ ድምፅ የተቀበለው መሆኑን ጠቁመው፤ ምክር ቤቱ ረቂቅ አዋጁን እንዲያፀድቀው ጠይቀዋል፡፡

ምክር ቤቱም በቀረበው የረቂቅ አዋጅ ማሻሻያ ላይ ከተወያየ በኋላ የኤሌክትሮኒክስ ፊርማ አዋጅ ቁጥር 1072/2010 ማሻሻያ አዋጅ፤ አዋጅ ቁጥር 1358/2017 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አፅድቆታል፡፡

# ባህላዊ የአጥንት ሕክምናና...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

መሠረት በተለይ ወደ ጤና ተቋማት ከመጡ ሰዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ ዘርፈ ብዙ የጤና ችግሮች እንደታየባቸው ተረጋግጧል፡፡

ወደ ጤና ተቋም ከመጡት ውስጥ 77 ከመቶ ያህሉ እንዲሁም በማህረሰብ ውስጥ ያሉ 68 ከመቶ ያህሉ የጎንዮሽ ጤና ጉዳት እንዳላቸው ያብራራሉ፡፡

በጥናቱ መሰረት በባህላዊ የአጥንት ህክምና /ወጌሻ/ ምክንያት በሰዎች ላይ የሚከሰቱ የጎንዮሽ ጤና ጉዳቶች ዋነኛ መንስኤዎች ሁለት መሆናቸውን ዶክተር መንግስቱ ይጠቅሳሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው መንስኤ አላስፈላጊና ተደጋጋሚ ማሸት መሆኑን ይናገራሉ፡፡ አንድ ሰው መገጣጠሚያውም ሆነ ጡንቻው ከተጎዳ በኋላ በተደጋጋሚ በሚታሸበት ጊዜ የመዳን ሂደቱን እንደሚያዘገየው ያስረዳሉ፡፡ ይኸው አላስፈላጊና በድግግሞሽ ማሸት ታማሚዎች ቋሚ ህመም እንዲኖራቸው፣ ከህመማቸው ቶሎ እንዳያገግሙ፣ እንዲያብጥ፣ መንቀሳቀስ እንዳይችሉ፣ እጃቸውንና እግራቸውን መጠቀም እንዳይችሉ እንደሚያደርጋቸውም ነው ዶክተር መንግስቱ የሚናገሩት፡፡

ሁለተኛው የጎንዮሽ ጤና ጉዳት መንስኤ አጥብቆ ማሰር መሆኑ በጥናቱ እንደተመላከተ ዶክተር መንግስቱ ይጠቁማሉ፡፡ በተለይ የጎንዮሽ ጉዳቶቹ ጊዜያዊና ቋሚ የሆነ የአካል ጉዳት፣ ጋንግሪን ፈጥሮ እግርና እጅን ማጣት ብሎም ሞት የሚያስከትል ከሆነ በአብዛኛው መንስኤው አጥብቆ ከማሰር ጋር የሚገናኝ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

እጅና እግር ለረጅም ጊዜ ጠብቆ ሲታሰር የደም ዝውውር የማያገኝ ከሆነ እጅ ወይም እግር በስብሶ ለጋንግሪን በሽታ እንደሚያጋልጥ ይገልፃሉ። የሰውነት መበስበስ ከመጣ ደግሞ ህይወትን ለአደጋ ስለሚጥል የበሰበሰውን አካል በቀዶ ህክምና ማስወገድ የመጨረሻው አማራጭ እንደሚሆንም ነው ዶክተር መንግስቱ የሚያስረዱት፡፡

ይህ ሀገር አቀፍ ጥናት ከመካሄዱ በፊት በሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች የተጠኑ ጥናቶች ከባህላዊ የአጥንት ህክምና /ወጌሻ/ ጋር በተገናኘ በርካታ የጎንዮሽ ጤና ጉዳቶች እንደነበሩ ማሳየታቸውን ዶክተር መንግስቱ ያስታውሳሉ፡፡ ከእነዚህ የጎንዮሽ ጤና ጉዳቶች መካከል እግርና እጅን ማንቀሳቀስ አለመቻል፣ የጡንቻ መሟሸሽና ከጥቅም ውጪ መሆን፣ የስብራት አለመዳንና፣ ኢንፌክሽንና ጋንግሪን መፈጠር ብሎም ለሞት የሚዳርግ መሆኑ እንደሚገኙበት ያብራራሉ፡፡

ከዚህ በፊት በባህላዊ አጥንት ህክምና /ወጌሻ/ ምክንያት ሲከሰቱ የነበሩ የጎንዮሽ የጤና ጉዳቶች መኖራቸው ሀገር አቀፍ ጥናቱን ለማካሄድ መነሻ እንደሆነም የጠቆሙት ዶክተር መንግስቱ፤በባህላዊ የአጥንት ህክምና /ወጌሻ/ መንስኤ የሚከሰቱ የጎንዮሽ ጤና ጉዳቶችን ለመቅረፍ ጥናቱ የተለያዩ መፍትሔዎችን ማመላከቱን ያነሳሉ፡፡

በጥናቱ መሰረት በአብዛኛው ለዚህ የጎንዮሽ ጉዳት ተጋላጭ ሕፃናት በመሆናቸው በተለይ ትምህርት ቤት አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች ማለትም ልጆች፣ ወላጆች፣ መምህራንና ሌሎች አካላት የተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን አማራጮችን በመጠቀም ስለጉዳዩ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ፣ ማህበረሰቡን ማንቃትና መከላከል ላይ መስራት አንዱና ዋነኛው በጥናቱ የተመላከተ መፍትሄ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡

በሌላ በኩል አደጋ ሲያጋጥም ከሚያሹና አጥብቀው ከሚያስሩ አካላት በተለይም ከባህላዊ የአጥንት ህኪሞች /ወጌሻዎች/ ጋር ምክክር ማድረግና ስልጠና መስጠት፣ አሰራራቸውን እንዲያዘምኑ ማድረግ የጎንዮሽ ጤና ጉዳቱን ለመቀነስ በጥናቱ እንደመፍትሄ ከተቀመጡ ነጥቦች ውስጥ ሁለተኛው መሆኑን ዶክተር መንግስቱ ይናገራሉ፡፡

ሰዎች የአጥንትና መገጣጠሚያ ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ጤና ተቋማት እንደሚመጡ የሚናገሩት ዶክተር መንግስቱ፤ ችግራቸው በትክክል ባለመታወቁ ከአራቱ አንዱ መጀመሪያ ወደ ጤና ተቋም መጥተው ከዚያም ወደ ባህላዊ የአጥንት ህክምና/ዊጌሻ/ እንደሄዱ ጥናቱ ማሳየቱን ያመለክታሉ፡፡ ይህም በጤና ተቋማት በኩል ችግሮች መኖራቸውን ጥናቱ እንደጠቆመና ጤና ተቋማትን፣ የተለያዩ የጤና ባለሙያዎችን፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን ማብቃትና ማሰልጠን ለዚህ ችግር መፍትሄ መሆኑን እንዳመላከተ ይጠቁማሉ፡፡

በባህላዊ የአጥንት ህክምና /ወጌሻ/ መንስኤ ለሚከሰቱ የጎንዮሽ ጤና ጉዳቶች አብዛኛዎቹ ሰለባዎች ሕፃናት መሆናቸውን ዶክተር መንግስቱ አንስተው፤ እነዚህ የጤና ጉዳቶች በዚሁ ከቀጠሉና መፍትሄ ካልተበጀላቸው የጤና ጉዳቱ ቀላል እንዳልሆነ ይገልፃሉ፡፡ በተለይ ቋሚ የአካል ጉዳት የሚያስተናግዱ ሕፃናት እንደሚበዙ ያመለክታሉ፡፡ ይህንኑ ተከትሎ በቤተሰብም ሆነ በሀገር ደረጃ የኢኮኖሚ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ውጤቱ እንደ ሀገር የምንኮራበት ትልቅ ስኬት ነው!

ሀገራችን የዓባይ ወንዝ ውሃን በኃላፊነት እና በፍትሐዊነት ለመጠቀም የሚያስችል አዲስ የትብብር ማሕቀፍ ለመፍጠር ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ሰፋፊ ጥረቶችን ስታደርግ ቆይታለች። በብዙ ውጣ ውረድ እና ፈተናዎች የተሞላው ጥረቷ አሁን ላይ ፍሬ አፍርቶ በወንዙ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ታሪካዊ ምዕራፍ ላይ ተደርሷል።

ሀገራችን ለናይል ወንዝ 80 ከመቶ የሚደርሰውን የውሃ መጠን ከማበርከቷ አኳያ፤ ከወንዙ ውሃ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በቀደሙት ዘመናት ሆነ አሁን ላይ የሚነሱ አጀንዳዎች በብዙ መልኩ ይመለከቷታል ።በተለይም የወንዙን ውሃ በፍትሐዊነት ለማልማት ያላትን መሻት ለመተግበር በምታደርገው ጥረት ውስጥ ለጉዳዩ የምትሰጠው ትኩረት ከፍ ያለ ነው።

ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን በተመለከተ በሀገራትም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረሱ ስምምነቶችም ሆኑ፤ ስምምነቶቹ የሚገዙለት አስተሳሰብ ፍትሐዊነትን መሠረት ያደረገ እና ለዚሁ የተገዛ ነው። በእነዚህ ወንዞች አጠቃቀም ዙሪያ የሚነሱ የትኛውም አይነት ጥያቄዎችም ተገቢውን ምላሽ ሊያገኙ የሚችሉት ይህንኑ እውነታ ታሳቢ ባደረገ መንገድ ነው።

በተለይም ፍትሐዊነት ዓለም አቀፍ መርህ በሆነበት በዚህ ዘመን፤ በድንበር ተሻጋሪ ወንዞች የውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የሚነሱ ጥያቄዎች፤ ዘላቂ እና ሁሉንም ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል ምላሽ ማግኘት የሚችሉት ዘመኑን በሚዋጀው የፍትሐዊነት እሳቤ ሲገሩ ብቻ ነው።

ከዚህ ውጪ የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ የወለዳቸው ፣ በአንድም ይሁን በሌላ የቅኝ ገዥዎችን ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ለማስፈጸም ተግባራዊ የሆኑ ፣ የሀብቱ ባለቤት የሆኑ ሕዝቦች ውሳኔ የሌለባቸውን ውሎች ስምምነቶችን ታምኖ በእነርሱ ላይ ቆሞ ለመራመድ መሞከር ከዘመኑ ጋር በተቃርኖ ከማቆም ባለፈ፤ የቅኝ ገዥዎች አስተሳሰብ ሰለባ መሆን ጭምር ነው።

የናይል ወንዝ የተፋሰሱ ሀገራት የጋራ ሀብት ነው። ከአንተ በላይ ለእኔ ያስፈልገኛል፤ ከአንተ በላይ ለኔ የህልውናዬ መሰረት ነው ... ወዘተ የሚሉ፤ ከዘመናት በፊት የነበረ ማኅበረሰብ የፈጠራቸው ስጋቶች፤ ባለንበት የሰለጠነ ዓለም ትርጉም የሚሰጥ የአደባባይ መደራደሪያ ሊሆን አይችልም።

የናይል ወንዝ ውሃ አጠቃቀም የተፋሰሱ ሀገራት አሁናዊ ትልቅ አጀንዳ ነው። አብዛኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት ሕዝቦች ካሉበት ድህነት እና ኋላቀርነት በልማት ለመውጣት ለሚያደርጓቸው ጥረቶች የወንዙ ውሃ አንዱ የመልማት አቅማቸው ነው። ይህን ተፈጥሯዊ አቅማቸውን በፍትሐዊነት መጠቀም የማንንም ይሁንታ የማይጠብቅ መብታቸው ነው።

ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በሀገራችን አነሳሽነት ተግባራዊ የሆነው የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍ ዋነኛ ዓላማም ይሄው ነበር፤ የወንዙን ውሃ በፍትሐዊነት እና በኃላፊነት መጠቀም የሚያስችል የጋራ መግባባት ላይ መድረስ፤ የቅኝ ገዥዎች ጥላ ያጠላባቸውን የቀደሙ ውሎች ዘመኑን በሚመጥን ስምምነት መለወጥ ዋነኛ ግቦቹ ነበሩ።

እንዲህ አይነት ጥረቶች ባለንበት ዘመን እና ዘመኑ ከሚገዛበት አስተሳሰባዊ ልቀት አኳያ፤ ብዙ የማያለፉ ፤ በቀላሉ ስኬታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ቢታመንም ፤ከተፋሰሱ የታችኛው ሀገራት፤ በተለይም በግብጽ በኩል ካለው የአስተሳሰብ ዝንፈት ብዙ ፈተናዎችን ለማለፍ ተገድዷል።

የግብጽ መንግሥት ገና ከጅምሩ በአንድ በኩል የተፋሰሱ ሀገራት በወንዙ ፍትሐዊ አጠቃቀም ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ እንዳይደርሱ፤ ከዚያም አልፎ የፍትሐዊነት እሳቤ የተፋሰሱ ሀገራት አጀንዳ እንዳይሆን ረጅም ርቀት ተጉዟል።

በቅኝ ገዥዎች የተቀመጡ ኢፍትሀዊ ውሎች/ስምምነቶችን ለማስቀጠል ፣ የተለያዩ ትርክቶችን በመፍጠር የገዛ ሕዝቡን ጨምሮ ዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ በወንዙ ውሃ አጠቃቀም ዙሪያ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያለ እረፍት ሠርቷል ። በተፋሰሱ ሀገራት ሉዓላዊ መብት ላይ ያልተገባ ጫና ለመፍጠርም በስፋት ተንቀሳቅሷል።

አብዛኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት በግብጽ በኩል የተፈጠሩ ጫናዎችን እና የመከፋፈል ሴራዎችን በጽናት ተሻግረው ፣ የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍን ፈርመው በሀገራቸው ደረጃ የሕጋቸው አካል አድርገዋል። በዚህም ለፍትሐዊነት ያላቸውን የጸና አቋም በአደባባይ አሳውቀዋል።

ሀገራችን የላይኛው የተፋሰሱ ሀገር ብትሆንም ጉዳዩ ፍትሐዊ እንዲሆን ለማድረግ እና ማሕቀፉ ስኬታማ እንዲሆን ከሌሎቹ ሀገራት ጋር በጋራ ስትሠራ ቆይታለች። ተሳክቶላትም ማሕቀፉ አስገዳጅ ሕግ ወደሆነበት ታሪካዊ ምዕራፍ ተሸጋግሯል። ውጤቱም እንደ ሀገር ያሳካነው እና የምንኮራበት ትልቅ ስኬት ነው።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ለልማቱ ስኬት የተሳለጠ አማራጭ የትራንስፖርት ስምሪት

**ሜሴዲ ከኳስ ሜዳ**

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካ ህብረት መዲና እንዲሁም የዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ የሆነችው አዲስ አበባ እንደ ስሟ ውብ ልትሆን ፣ እንደ ተሰጣትም ኃላፊነት ዓለም አቀፋዊነቷን መጠበቅ ያስችላት ዘንዳ ራሷን ማደስ ከጀመረች ወራትን አስቆጥራለች። በእነዚህም ጊዜያት ባከናወነችው የኮሪደር ልማት ሥራ ነዋሪዎቿን ብቻ ሳይሆን የዓለም አቀፍ ማህበረሰቡንም ጭምር አድናቆት ያተረፈ ፈጣን ለውጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ አስመዝግባለች፤ እያስመዘገበች ትገኛለች።

በዚህ የልማት ሥራ ውበትን ብቻ ሳይሆን ለነዋሪዎቿ ምቹ የመኖሪያ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችሉ ተግባራትን አከናውናለች። ከዚህም ባለፈ ከተማይቱ ትልቅ የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን ያለሙ ግንባታዎችንም እያካሄደች ነች። በቦሌ፣ በሜክሲኮ፣ በአራት ኪሎ፣ ፒያሳና በሌሎችም አካባቢዎች ተጠናቀው ለአገልግሎት ክፍት በሆኑ መንገዶች ላይ የተስተዋሉት የልማት ሥራዎች ‘ይበል' የሚሰኙና የሚያኮሩ ናቸው።

ነዋሪው እየተከናወነ ባለው የኮሪደር ልማት ሥራ እጅግ ደስተኛ መሆኑን፤ ልማቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ እየገለጸ ይገኛል። ይህንን የሕዝብ የልማት ጥያቄ የተረዳው የከተማ አስተዳደሩም ሁለተኛውን ዙር የልማት መርሀ - ግብር በተለያዩ የከተማይቱ አካባቢዎች አስፍቶ የቀጠለ ሲሆን፤ ግንባታውም ልክ እንደ መጀመሪያው ሁሉ ቀን በሌሊት እየተከናወነ መሆኑን ለማስተዋል ችለናል። በተለይም ሁሉም የመሠረተ ልማት ተቋማት በቅንጅት መሥራታቸውን የቀጠሉ መሆኑ ሀገር ከዚህ ቀደም ታወጣ የነበረውን ያልተገባ ወጪ የሚታደግ እንደሆነ እሙን ነው።

በሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት ሥራዎች በቅንጅት ሌት ተቀን እየተጋ ባለበት ሁኔታ ግን የትራንስፖርት ስምሪቱ ላይ እምብዛም ትኩረት የተሰጠው አለመሆኑን በቀን ተቀን ጉዞዬ ለማስተዋል ችያለሁ። ይህንን ለማለት ያነሳሳኝ ደግሞ ከተለያዩ የመዲናዋ አካባቢዎች የሚመጡ አሽከርካሪዎች እንደ ዋነኛ መሸጋገሪያ የሚጠቀሙባቸው የጎሮና የጃክሮስ አደባባይ አሰልቺ እና አማራሪ የትራፊክ ጭንቅንቅ ነው።

እነዚህ መንገዶች ወትሮም ቢሆን በየእለቱ በርካታ ተሽከርካሪዎች የሚስተናገዱባቸው ከመሆናቸውም ባሻገር በተለይ ጠዋትና ማታ አማራጭ ካልጠፋ በስተቀር ለመጠቀም የማይመረጡ፣ አደባባዮቹን ብቻ ለመሻገር ለሰዓታት የሚቆምባቸው መሆናቸውን ተጠቃሚዎች የሚመሰክሩት ሀቅ ነው።

አስቀድሜ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ይህ አካባቢ (ከጎሮ አደባባይ እስከ መገናኛ) በኮሪደር ልማቱ ሁለተኛው ምዕራፍ ተካተው የመልሶ ማልማቱ ሥራ እየተከናወነ ካለባቸው ሥፍራዎች አንዱ ነው። ይህ መንገድ ተጠናቆ አገልግሎት ላይ ሲውል የነበረው መጨናነቅ ቀርቶ ልክ እንደቀደሙት የኮሪደር ልማት መርሀ-ግብሩ መንገዶች እፎይታን የሚሰጡ እንደሚሆኑ አያጠያይቅም። ይሁንና ይህ መንገድ ነባርና ከፍተኛ ኢኮኖሚ የሚንቀሳቀስበት እንደመሆኑ ግንባታው ሙሉ ለሙሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ አማራጭ መንገድ ማበጀት ያለመቻሉ በነዋሪውም ሆነ በልማቱ ላይ ጫና እየፈጠረ ነው የሚል እምነት አለኝ።

ምክንያቱ ደግሞ በኮሪደር ልማቱ በአስፋልት ዳር ላይ የነበሩ ቤቶች እና የንግድ ተቋማት እየፈረሱ፤ ቁፋሮና የተለያዩ ሥራዎች እየተከናወኑ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ፍርስራሾቹ በአብዛኛው የእግረኛ መንገድ ላይ ፈሰዋል፤ በፍጥነት እየተነሱም ባለመሆኑ እግረኛውን ለትራፊክ አደጋ በሚያጋልጥ መልኩ ከተሽከርካሪዎች ጋር እየተጋፋ ለመሄድ ተገዷል። ተሽርካሪዎችም ቢሆኑ ድሮም የጭንቅ መንገድ በሆነው በዚህ መስመር ያገኙትን ክፍተት ሁሉ ተጠቅመው ለማለፍ ሲሞክሩ ለአደጋ የሚጋለጡበትንም ሁኔታ አስታውያለሁ።

በእርግጥ በዚህ መስመር ለአውቶቡስ ብቻ የተፈቀደ መንገድ መኖሩ በተለይ ለብዙኋኑ አውቶቡስ ተጠቃሚ እፎይታ የሚሰጥ ነበር፤ ይሁንና አብዛኞቹ ታክሲዎች እና የቤት አውቶሞቢሎች መጨናነቁን ለመሸሽ ሲሉ ሕግ ጥሰው በአውቶቡስ መስመር ሲጠቀሙ ይታያል፤ ሌሎቹም በዳር በዳር ያሉ አቋራጭ መንደሮች ውስጥ ለመግባት ጥረት ሲያደርጉ ከአውቶቡሶቹ ጋር አላግባብ ግፊያ ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታም አለ። ይህም አጠቃላይ በአካባቢው የትራፊክ ፍሰቱ ላይ እየፈጠረ ካለው ጫና ባሻገር በአውቶቡስና በታክሲ ወይም በቤት አውቶሞቢል አሽከርካሪዎች በመንገድ ይገባኛል ንትርክ ተሳፋሪዎች ለእንግልት ሲዳረጉ ማየትም የእለት ተእለት ገጠመኛችን ሆኗል።

መቼም ይህ ሁሉ ሲሆን ትራፊክ አልያም የመንገድ ትራንስፖርት ባለሙያዎች እንዴት በአካባቢው የሉም? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም። ልክ ነው፤ ሁሉም አሉ፤ ግን ደግሞ አብዛኞቹ ተሽከርካሪዎችን በፍጥነት አስተናብረው ፍሰቱ እንዲቀንስ ከማድረግ ይልቅ፤ ከአሽከርካሪዎቹ ጋር ባለ ንትርክ ሳቢያ ተጨማሪ መጨናነቅ ሲፈጥሩ ታዝቤያለሁ።

ከቅጣት ይልቅ አማራጭ የሆኑ መንገዶችን በመጠቀም ችግሩ እንዲቃለል የማድረጉ ዝንባሌም እምብዛም አይስተዋልም። አልፎ አልፎም የትራፊክ መብራት የማይሰራበት ሁኔታ ከመኖሩም ባሻገር ትራፊኮቹ በራሳቸው ሲያስተናብሩ የበለጠ መጨናነቅ ላለበት አቅጣጫ ትኩረት ስለማይሰጡ ችግሩን ከድጡ ወደማጡ እንዳደረገውም ግልፅ ነው።

በሌላ በኩል ከዚህ ቀደም ግንባታው ገና ባልተጠናቀቀው የጎሮ ቦሌ መንገድ ተሽከርካሪዎች እንዲጠቀሙ መደረጉ የነበረውን ጫና በማቃለል ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው። በተለይ ከቱሉዲምቱ ፣ ከሲሚሲና ሰሚት አካባቢዎች መጥተው ነባሩን የጎሮ መንገድ የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች እንደልብና ባሰቡት ጊዜ የሚደርሱ መሆኑ ይህንን ያልተጠናቀቀ መንገድ ምርጫቸው አድርገውት ነበር። ሆኖም ልክ ሁለተኛው ምዕራፍ ሲጀመር የአዲሱ መንገድ ግንባታም በመቀጠሉና መንገዱ በመዘጋቱ ምክንያት ጫናው በዚያው በነባሩ መንገድ ላይ እንዲያርፍ ሆኗል።

እኔም ሆንኩኝ አብዛኛው የዚያ መንገድ አዘውታሪ የመንገዱ ግንባታ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት እስኪጀምር በተስፋና በጉጉት እንጠብቃለን። የምንናፍቀው ልማት እውን እስኪሆን ድረስ ግን አሁን እየተጋፈጥነው ያለውን እንግልትና ስቃይ ይቀርልን ዘንዳ ሌሎች የመፍትሔ አማራጮቹ ቢዘረጉ መልካም ነው ባይ ነኝ። በተለይም ደግሞ ከዚህ ቀደም አገልግሎት ላይ ውሎ የነበረውና ያልተጠናቀቀው አዲሱ የጎሮ ቦሌ መንገድ የጎሮ መገናኛው የኮሪደር ልማት እስኪጠናቀቅ ድረስ ለተሽከርካሪዎች ክፍት ቢሆን አሁን ያለውን ጫና በማቃለል ረገድ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል።

በተጨማሪም ደግሞ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን ክፍት በማድረግና ለአሽከርካሪው በመጠቆም እንዲጠቀሙበት ማድረግ ይገባል። በከተማ ያለውን የትራንስፖርት ስምሪት በተሳለጠ መልኩ ማካሄድ በተቻለ ቁጥር የተጀመረው ልማት ከግብ እንዲደርስ ከማድረግ አኳያም ፋይዳው የሚናቅ አይደለም ስል ማስገንዘብ እወዳለሁ።

# በክንፎቹ ከፍታውን በብቃቱ ሽልማቶችን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የኢትዮ ጂቡቲ ባቡር መንገድ ሠራተኛ የሆኑት ኢንጂነር ሰለሞን ሁሉቃ፤ ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ የኢትዮጵያ ስም ይነሳ የነበረው ከድህነት ጋር የተያያዘ ነው ይላሉ፡፡

ኢንጂነር ሰለሞን፤ በአፍሪካም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓለም አደባባይ ሽልማት አገኘ ማለት ያገኘው አየር መንገዳችን ብቻ አይደለም፤ ያሸነፈችው ኢትዮጵያ ራሷ ናት ይላሉ።

ሽልማቱ አየር መንገዳችን ትናንት በትጋትና በታታሪነት ባስመዘገበው ውጤት የመጣ ሲሆን፤ ለነገ ቱሪስቶችም ሆነ የተለያዩ መንገደኞች የኢትዮጵያን አየር መንገድ ምርጫቸው እንዲያደርጉ የሚጋብዝ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የኢትዮጵያን አየር መንገድ ብዙዎች ምርጫቸው አደረጉ ማለት ደግሞ ለኢትዮጵያ ገቢዋን የሚያሳድግ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ሌላው ያነጋገርናቸው የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አምባሳር ጥሩነህ ዜና በበኩላቸው፤ አየር መንገዱ ያገኘው ሽልማት በብዙ መንገድ የሚተረጎም መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ለዚህም ምክንያታቸው ደግሞ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለኢትዮጵያ እያበረከተ ያለው ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ በመሆኑ ነው ይላሉ፡፡

አምባሳደር ጥሩነህ፤ አየር መንገዱ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ውጤት እያሳየ ነው፡፡ ወደ ስምንት አስርት ዓመታት ያህል እድሜ ያስቆጠረ አየር መንገድ በአፍሪካ ውስጥ ምናልባት ከግብጽና ደቡብ አፍሪካ በስተቀር በወቅቱ ሌሎች ሀገሮች የራሳቸው አየር መንገድ አልነበራቸውም ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ግን ቀድመው የተመሰረቱ ሁለቱን ሀገራት ጨምሮ በአፍሪካ ካሉ አየር መንገዶች ሁሉ በልጦ እያንጸባረቀ ያለ ታላቅ አየር መንገድ መሆን ችሏል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመሸለሙ ፋይዳ አንደኛ በገቢ ደረጃ ሲሰላ ለኢትዮጵያ የሚያስገኘው ገቢ ከፍተኛ ገንዘብ ነው፡፡ ይህም የሚሰላው በብዙ ቢሊዮን ብር ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያ ከቱሪዝምም ሆነ ከሌላው ዘርፍ ከምታገኘው ገቢ ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ በመሆኑ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ያመለክታሉ፡፡

ኢንጂነር ሰለሞን፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስመ ጥር ሆነ ማለት የተለያዩ ሀገራት ተጓዦች በኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡ አየር መንገዱ ተሸለመ ማለት ብዙዎቹ ተጓዦች በኢትዮጵያ አየር መንገድ እምነት እንዲያደርጉ አደረገ ማለት ነው ይላሉ፡፡

ተጓዦች የኢትዮጵያን አየር መንገድ ምርጫቸው የማድረጋቸው ምክንያት ሲገልጹም፤ ተጓዦች ምቾት ተሰምቷቸው እንዲጓዙ ስለሚፈልጉ ስመ ጥሩ የሆነውን የኢትዮጵያ አየር መንገድን ተመራጭ ያደርጋሉ ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ ብዙዎች መረጡት ማለት ኢትዮጵያ ተጠቃሚ ሆነች ማለት ነውና በተዘዋዋሪ ገቢዋን ከፍ አደረገች እንደማለት መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ኢንጂነሩ እንደሚሉት፤ አየር መንገዱ የኢትዮጵያውያን መገለጫ ብራንድ ነው፡፡ በመሆኑም በየመዳረሻው ኢትዮጵያን አስተዋዋቂና በኢትዮጵያ ላይ እምነት እንዲጣል ጉልህ ድርሻ አለው፡፡

አየር መንገዱ ለተከታታይ ጊዜ ለመሸለም ያበቃው ትልቁ ምክንያት በተቋሙ ከፍ ያለ ትብብር በመኖሩና ትልቅ መዋቅርም በመዘርጋቱ ነው ይላሉ። በመሆኑም አየር መንገዱ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካም ኩራት ነው ሲሉም ያመለክታሉ፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ በተቋሙ ጥብቅ የሆነ የሥራ ባህል አለ፤ መንግሥት ሲቀያየር እንደሌሎቹ ተቋማት የሚለዋወጥ አይደለም፡፡ መንግሥት ተቀያየረ አልተቀያየረ ሥርዓቱ ሳይፋለስ ሥራውን በአግባቡና በእኔነት ስሜት የሚሠራ ተቋም በመሆኑ ወጥነት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም አየር መንገዱ በየሥርዓቱ የራሱን ጥንካሬ ይዞ እየተጓዘ ያለ ተቋም ነው፡፡

እንደ አየር መንገድ ተቋም አመርቂ ሥራ ሰርቶ ስመ ጥር ተቋም ለመሆንና ኢትዮጵያን ከፍ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆን የግድ ነው የሚሉት ኢንጂነር ሰለሞን፤ እንዲያውም በአየር መንገዱ የሚሰጥ ስልጠና እኔ ባለሁበት ተቋምም እንዲሰጥ ፍላጎት አለኝ ብለዋል። ለዚህ ምክንያታቸው ደግሞ በአየር መንገዱ ውስጥ የሚሰጡ ስልጠናዎች በአግባቡ ወስዶ ለቦታው ብቁ ሆኖ መገኘት የግድ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አምባሳደር ጥሩነህ፤ ልክ እንደ ኢንጂነሩ ሁሉ አየር መንገዱ የሚያስገኘው ገቢ ከፍ ማለቱ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ስም በዓለም አደባባይ በከፍተኛ ደረጃ የሚያንጸባርቅ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ ከአፍሪካ ሀገሮች ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር የሚነጻጸር የለም። አየር መንገዱ ሳያቋርጥ ለተከታታይ ዓመታት የሚሸለምና ትርፋማ እየሆነ የመጣ ነው፡፡ የአፍሪካ አየር መንገዶች የኢትዮጵያን ያህል ውጤታማ ሊሆኑ ቀርቶ ጥቂት ትርፍ ማምጣታቸው ብቻ እንደ ትልቅ ዜና የሚቆጠርላቸው መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አየር መንገድ እያሰበ ያለውን እየተገበረ የሚገኝ ነው። ከሌሎች አየር መንገዶች ጋር በመተባበር፣ በመቀናጀትና ግማሹን ደግሞ በግዥ በመውሰድ ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮችን አየር መንገድ ለማስፋፋት ነው። ይህ ጥረቱ ደግሞ በጣም የሚያስገርም ነው ሲሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ተናግረዋል፡፡

የአየር መንገዱ መሸለም ከሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ጎን ለጎን ሌላም ፋይዳ አለው ሲሉ ጠቅሰው፤ በተለይም መንግሥት የሚመራው ይህ ግዙፍ ተቋም ባስመዘገበው አመርቂ ውጤት ተከታታይ የሆነ ሽልማት ማግኘቱ ወደግል ይዛወር እያሉ የሚወተውቱትን የዓለም ባንክና ምዕራባውያኑን ቆም ብለው እንዲያስቡ የሚያደርግ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የኢትዮጵ አየር መንገድ በመንግሥት እጅ የሚተዳደር ሆኖ በአፍሪካ ከዚያም አልፎ ከብዙ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ተወዳድሮ ብልጫ ያገኘ ተቋም መሆን ችሏል ሲሉ አስረድተዋል፡፡ ተቋሙን ያቋቋመው መንግሥት ሲሆን፤ ንብረትነቱም የመንግሥት በመሆኑ መንግሥት እንዲህ አይነት ውጤታማ ሥራ መሥራት አያስችለውም የሚለውን አባባል ሽልማቶቹ በይፋ ውድቅ ማድረጋቸውን ያስመሰከሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ መንግሥት እየመራ ያለው አየር መንገድ ውጤታማ ከመሆኑም ባሻገር የትኛውም አካል የመሰከረለት ስለመሆኑ የአደባባይ ምስጢር ስለሆነ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አምባሳደር ጥሩነህ እንዳሉት፤ አየር መንገዱ ብዙ ፈተናዎችን አልፎ እዚህ ደርሷል፡፡ ሌሎቹ እንደ እሱ ለምን ውጤታማ አልሆኑም ብሎ ማሰብም ጥሩ ነው፡፡ እንዴት አድርገን እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ አዋጭና ስመ ጥር መሆን እንችላለን ከተባለ ብዙ ርቆ መሔድ ሳያስፈልግ የኢትዮጵያውያን ኩራት ከሆነው አየር መንገድ ብዙ ነገር መማር ይቻላል፡፡ ፈለጉንም መከተል ሕዝብንም ሀገርንም በጣም ተጠቃሚ ያደርጋል፡፡

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ከስምንት አስርት ዓመታት በፊት በአጼ ኃይለ ሥላሴ የተመሠረተው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ በፈጣን እድገቱ በአፍሪካ ስመ ጥር ነው፡፡ አየር መንገዱ አፍሪካን ከዓለም፤ ዓለምን ከአፍሪካ በማስተሳሰርም ስሙን ገንብቷል። ዋና መናኸሪያውን አዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ላይ አድርጎ፤ በቶጎ ሎሜ፣ በማላዊ ሊሎንፍዌ፣ በዛምቢያ ሉሳካ ተጨማሪ መናኸሪያዎችን ከፍቷል።

የአፍሪካን መንገደኞች እና ጭነቶችን በማጓጓዝ ከአህጉሪቱ የአየር ትራንስፖርት ገበያ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዘው አየር መንገዱ፤ ዘመናዊ በሆኑ አውሮፕላኖች በአምስት አህጉራት ከ150 በላይ ወደ ሆኑ መዳረሻዎቹ ይበራል።

የቦይንግ፣ የኤርባስ እና የቦምባርድኤር ምርት የሆኑ የተለያዩ አውሮፕላኖች ያሉት የኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ በአጠቃላይ 148 አውሮፕላኖችን በአየር ላይ በማሰማራት በአፍሪካ ውስጥ ተፎካካሪ የሌለው ለመሆን ችሏል። በየዓመቱ በቢሊዮኖች ዶላር የሚቆጠር የውጭ ምንዛሪን ለሀገሪቱ ያስገኛል።

መረጃ ያጋሩን ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ፤ መንግሥት ሌሎቹን ተቋማት እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ጎልተው እንዲወጡ ግፊት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ሌሎችም ተቋማትም ከአየር መንገዱ የስኬቱን ምስጢር መማር ይጠበቅባቸዋል፡፡

አየር መንገዱ አሁን ያለበት ሁኔታ ጥሩ ሲሆን፤ ወደፊት በራሱ ብራንድ መገለጥ የሚችልበት ጊዜ ሩቅ አይሆንምና ያንን ግብ ለማሳካት በጀመረው ሂደት ይቀጥላል፡፡ የራሱንም አውሮፕላን የሚያመርትበት ስትራቴጂ ቀይሶ ውጤታማ እንድንሆን ውድድሩን ከወዲሁ ከፍ ማድረግ ይኖርበታል ሲሉ ምሁራኑ ምክረ ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡

# ‹‹መሪነት ሀገርን ከድህነት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ‹‹ነጸብራቅ›› የመሪነት ኮንፍረንስ በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ትናንት በተካሄደ ወቅት እንደገለጹት፤ መሪነት ለትውልድ መሥራት እንደሆነ እና ሀገርን ከድህነት ወደ ብልፅግና የማሻገር ርዕይ ያነገበ የትውልድ አደራ ነው፡፡ የአመራር ከፍተኛው ጥራትም ታማኝነት ነው፤ አመራሩ ለራሱ፣ ለሕዝቡና ለሀገሩ ታማኝ መሆን እንደሚገባውም ተናግረዋል፡፡

በመሪነት ኮንፍረንሱ ነባር አመራሩና ተተኪ አመራሩ ተሞክሮ ሲለዋወጡ መናበብ እንደሚፈጠር ገልጸው፤ አመራር ከተናበበ አንድ የአመራር ትውልድ የጀመረውን ሌላው የአመራር ትውልድ ይጨርሰዋል ነው ያሉት፡፡

ኢትዮጵያ በረዥም የታሪክ ምእራፍ ውስጥ አልፎ አልፎም ቢሆን ታላላቅ መሪዎችን አግኝታለች ያሉት አቶ ጥሩነህ፤ አመራሮቹን የሚተካቸው ጠፍቶ በአንድ ወቅት ብቅ ብለው የጠፉና ሊደገሙ የማይችሉ የጋን መብራት ሆነው ማለፋቸውን አስታውሰዋል፡፡

ይህንን አደራ የተቀበሉ ያላቸውን እውቀትና ክህሎት ሳይሰስቱ ጥቅም ላይ አውለው እዚህ አድርሰውታል ብለዋል፡፡ ቅብብሎሹን ለማስቀጠልና መንገዳችንን በመደመር ጉዞ ለማጽናት ቀሪው የዚህ ትውልድ ሥራ እንደሆነም አሳስበዋል፡፡

ዛሬ የተጀመሩት ንቅናቄዎችና የብልፅግና ሥራዎች ሁሉ ሊሳኩና ፍሬ ሊያፈሩ የሚችሉት የሚተክል፣ የሚያጠጣ ፣ የሚያሳድግ፣ የሚንከባከብና የሚሰበስብ አመራር በየዘመኑ ሲፈጠር እንደሆነም ጠቅሰዋል። እጅ ለእጅ ተያይዞ ለመጓዝ ዘመኑ የሚጠይቀውን የመሪነት ትጥቅ መታጠቅ ያስፈልጋልም ብለዋል፡፡

ነጸብራቅ የመሪነት ኮንፍረንስም የመጣንበትን፣ ያለንበትንና የወደፊት መዳረሻችንን እንዲያመላክት ታስቦ የተቀረጸ ስለመሆኑ ተናግረዋል፡፡ በተለያየ የሥራ መስክ ላይ ሆነን ያገኘናቸውን ልምዶች በማቀናጀት፣ ችግርን ወደ መልካም አጋጣሚ የቀየርንባቸውን ተሞክሮዎች በማጋራት፤ የመሪነት ጥበባችንን ለመለዋወጥ የሚያስችል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ነጸብራቅ የመሪነት ኮንፍረንስ እንደስሙ ሃሳቦች የሚንጸባረቁበት እንደሆነና በዲጂታል ዘመን የአመራሩን የተለየ ሚና ለመመልከት የሚያስችል ስለመሆኑ ጠቅሰው፤ ለሀገር ግንባታ በተለያየ ቦታ ላይ ያሉ አመራሮች ሚናም ምን መሆን እንዳለበት የሚመከርበት ኮንፍረንስ ነው ብለዋል፡፡

በተለይም በወጣቶችና በሴቶች ላይ በሚስተዋሉ ችግሮች እና በመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ኮንፍረንሱ ጊዜ ወስዶ የሚመክር እንደሚሆን አመላክተዋል፡፡

ኢትዮጵያ የህብረተሰቡን ድንቅ ሃሳብና ተግባር ተከትላ ትልም እንደምታስቀምጥና በብቁ አመራርና የህብረተሰብ ተሳትፎ ወደ ተግባርም እንደምትቀይር አቶ ተመስገን ተናግረዋል፡፡

ኮንፍረንሱ ከሀገሪቱ ከሁሉም ማዕዘናት የመጡ ልዩ ልዩ አመራሮችን ያቀፈ መሆኑ አድማስ ሰፊና ደርዘ ብዙ ያደርገዋል ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከሌሎች አፍሪካውያን ወንድሞች ጋር በቀጣይ ለሚመክረው ጉባዔም እርሾ ሆኖ እንደሚያገለግል ገልጸዋል፡፡

# የጥጥ ኮንትራት እርሻን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሚኒስቴሩ ሀገሪቱ ያላትን ጥጥ የማምረት አቅም ሥራ ላይ ለማዋልና ያለውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን እውን ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን አቶ ሳምሶን አስታውቀዋል፡፡

‹‹ምርታማነቱን ከማስፋትና በጥራት፣ በመጠንና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆነ የጥጥ አቅርቦት እንዲኖር ከማስቻል በዘለለ ከኢንዱስትሪው ጋር ጠንካራ ትስስር እንዲፈጠር ከክልሎችና ከመመለከታቸው ተቋማት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው›› ብለዋል፡፡

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በሀገሪቱ እየተመረተ ያለው ጥጥ ለሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች በቂ አይደለም፤ በዚህ ምክንያት ጥጥ ከውጭ እንዲመጣ እየተደረገ ነው፡፡ ‹‹ሚኒስቴሩ ከምርምር ተቋማት ጋር በመሆን የተሻሻሉ ዝርያዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በማውጣት ለተጠቃሚዎች ለማድረስ ጥረት እያደረገ ይገኛል። በተለይ አነስተኛ ማሳ ላላቸው አርሶ አደሮች የጥጥ አምራረት ኤክስቴንሽን እውቀትን የማሳደግ፣ ዘር ብቻ ሳይሆን ሌሎች የኬሚካል ግብዓቶችን በማቅረብ ምርታማነታቸው እንዲጎለብት እየተሰራ ነው፡፡

እንደ አቶ ሳምሶን ገለጻ፤ ጤናማ ባልሆነ የግብይት ሥርዓት ምክንያትና ተገቢው የግብይት ትስስር ባለመፈጠሩ ምክንያት ጥጥ አምራቹ ከፍተኛ የሆነ የገበያ ስጋት ስላለበት በስፋት ለማምረት ይቸገራል፡፡ በመሆኑም ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር የግብይት ሥርዓቱ ውጤታማ እንዲሆን የማድረግና እርሻውና ኢንዱስትሪው ተሳስረውና ተናበው የኮንትራት እርሻ ለማስፋት ርብርብ እያደረገ ይገኛል፡፡ የመሬት ሽፋኑንም ለማስፋት እየተደረገ ያለው ጥረት እምርታ እያመጣ ነው፡፡

በተጓዳኝም ከእርሻ እስከ ኢንዱስትሪ ድረስ ባሉ የእሴት ሰንሰለቶች ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር፤ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ለማርካት እየተሰራ መሆኑን አስገንዝበዋል። ‹‹የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎችን የጥጥ ፍላጎት በመጠንም፤ በጥራትም ሆነ በዋጋ ሙሉ ለሙሉ ሸፍነን ወደ ውጭ እስከመላክ ድረስ መሄድ የሚቻልባቸው ስራዎች እየተሰሩ ናቸው›› ብለዋል፡፡

እንደ ስራ አስፈፃሚው ማብራሪያ፤ በአሁኑ ወቅት በአማራ ክልል ምዕራብ ጎንደር ዞን የገንዳ ውሃ መዳመጫ የሚባል ፋብሪካ አካባቢ ካሉ 15ሺህ አርሶ አደሮች በኮንትራት ውል ወስደው በማምረት ለፋብሪካው ጥጥ እያቀረቡ ነው፡፡ በአርባ ምንጭ በሚገኙና ሌሎች የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎችም በእንደዚህ አይነት ስራዎች ውስጥ እንዲገቡ የኮንትራት እርሻ ህጉን ለማስተዋወቅ፤ ስጋቶች እንዲፈቱላቸው ለማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እየተሰሩ ናቸው፡፡ በርካታ ኢንዱስትሪዎች ከእርሻዎቹ ጋር የኮንትራት እርሻ ልማት ውስጥ ገብተው ሥራ ይጀምራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡


የጥጥ ምርታማነትን ለማሳደግና ከኢንዱስትሪው ጋር ለማስተሳሰር በሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ክልሎች ወሳኝ ሚና መጫወት እንዳለባቸው አስገንዝበው፤ ‹‹ለዚህም የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ለማካሄድ እየሰራን ነው፤ በዚህም ላይ በጣም ትልቅ ለውጥ እያመጣ ነው፤ የመሬት ሽፋኑም በዚያው ልክ ጭማሬ እየታየ ነው›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡ ‹‹ያንን ስንል ግን ነገሮች ሁሉ የተደላደሉ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ አሁንም በተለይ በግብይት፣ በግብዓትና በፋይናንስ አቅርቦት እንዲሁም በሰው ኃይል ላይ ብዙ መስራት ይጠበቅብናል›› ብለዋል፡፡

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የአባቷን ፈለግ የተከተለች - የዱዋላ ሌዘር መስራች

**ሰሚራ በርሀ**







ወጣት ረድኤት እጅጉ ትባላለች። ትውልድ እና እድገቷ አዲስ አበባ ነው። ገና ጀማሪ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ናት። የወጣትነት ጊዜዋን ውድነት ቀድማ የተረዳችው ትመስላለች።

ተማሪዎች የመሰናዶ የትምህርት ጊዜ ቆይታቸውን አጠናቅቀው ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሲገቡ ሰፊ የሚባል ጊዜ ይኖራቸዋል። ትምህርታቸው ላይ የሚኖራቸውን ውጤት ጥሩ ለማድረግ ሲሉም ሙሉ ለሙሉ ጊዜያቸውን ለትምህርታቸው ይሰጣሉ።

ወጣት ረድኤት እጅጉ በዛሬው የወጣቶች ገጻችን የነበራትን ጊዜ በአግባቡ በመጠቀም ስለመሰረተችው የራሷ ስራ እና አሁን ስላለበት ደረጃ አጋርታናለች። የእጅ ሙያ ባደገችበት ቤተሰብ ውስጥ የሚበረታታ ነው። በመሆኑም ወደ እዚህ ስራ ስትገባ ከወላጆቿ ጥሩ ድጋፍን አግኝታለች።

ረድኤት፣ የ12ኛ ክፍል ትምህርቷን አጠናቅቃ ሀገር አቀፍ ብሔራዊ ፈተና ወስዳ እረፍት ላይ ነበረች። የሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት ይፋ እስከሚደረግበት ጊዜ ድረስ ሰፊ የሚባል የእረፍት ጊዜ ነበራት። ታዲያ በዚህ ወቅት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ውጤታቸውን በጉጉት በመጠበቅ፣ ራሳቸውን በማዝናናት እና ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሲገቡ ይበልጥ ሊያግዟቸው የሚችሉ ትምህርቶችን በመማር ያሳልፋሉ። ረድኤት በዚህ ወቅት ቀድሞ ወደአዕምሮዋ የመጣው ምን ልስራ የሚለው ሀሳብ ነበር።

‹‹ወደእዚህ ስራ ልገባ የቻልኩት አባቴ ከቆዳ የሚሰሩ ጃኬቶችን ይሰራ ነበር ። በቤት ውስጥ ሙያውን በጥቂቱ አውቀው ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ብዙም ያልተለመደውን ለምን አልሰራም? የሚል ሀሳብ መጣልኝ።›› ትላለች። ከወላጅ አባቷ የወሰደችው ጥቂት ትምህርት ላይ በተቋም ደረጃ ስልጠና ወደሚሰጡ ማዕከላት ሄዳ ችሎታዋን ለማዳበር ወሰነች ።

የተለያዩ ቦርሳዎችን በማምረት እና ለገበያ በማቅረብ ስም ያተረፉ ድርጅቶች ምርቶቻቸውን ለገበያ የሚያቀርቡበት ዋጋ እጅግ ከፍተኛ የሚባል ነው። ቦርሳ አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች በእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው የሚገለገሉበት ነው። ይህንን ክፍተት የተረዳችው ረድኤት የተለያየ ዲዛይን ያላቸውን ቦርሳዎች በሰዎች ፍላጎት ላይ ተመስርታ በመስራት ስራዋን ለመጀመር ወሰነች።

‹‹ቦርሳ ለሴት ልጅ በጣም ወሳኝ ነው። እኔም በጣም እወዳለሁ። ቦርሳ እንደ ፋሽን በሀገራችን ውስጥ ገና ብዙ ሊሰራበት የሚገባ ነው።›› የምትለው ረድኤት፣ ሴቶች በማንኛውም ከቤት ውጪ ባለ እንቅስቃሴያቸው ቦርሳቸው አይለያቸውም። የሚይዙት ቦርሳም ያለው አገልግሎት ሊይዙት የሚፈልጉትን እቃ ከመያዝ ያለፈ ነው። ለሥራ፣ ለጉዞ እንዲሁም ለተለየ ፕሮግራም የሚያዘው ቦርሳ የተለያየ ነው። ከቤት ለመውጣት ያሰበች እንስትም እንዲሁ ያላትን ቦርሳ ይዛ አትወጣም። ከምትለብሰው ልብስ፣ ከምትገኝበት ኹነት ጋር የሚሄደውን ቦርሳ መርጣ ትይዛለች።

ባላት የእረፍት ጊዜ ተጠቅማ የምትፈልገውን ስልጠና ከወሰደች በኋላ በቤቷ ውስጥ በመሞከር ወደሥራው ገባች። ‹‹ቤተሰቦቼ ሙያ ያለው ሰው ወድቆ አይወድቅም ብለው ስለሚያምኑ አበረታተውኛል።›› በማለት የምትገልጸው ረድኤት፣ ሥራዋን በጀመረችበት ወቅት የቅርብ የምትላቸው ሰዎች ቦርሳዎችን እንደማበረታቻ እንድትሰራላቸው ይጠይቋት እንደነበር ታስታውሳለች።

ቀኑ ደርሶ የ12ኛ ክፍል፣ ሀገር አቀፍ ፈተና ይፋ ከተደረገ በኋላ ቀጣዩ ሒደት ተማሪዎች የተመደቡበትን የከፍተኛ የትምህርት ተቋም ማወቅ ነው። ‹‹ የተመደብኩት ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ነበር። በወቅቱ የነበረው የጸጥታ ሁኔታ ከባድ ስለነበር እዚሁ ለመማር ወሰንኩ ።›› ስትል ትናገራለች።

አሁን ላይ በቢዝነስ ማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪ ናት ። በኮሜርስ በምሽት መርሀግብር እየተማረች ቀን ቀን ደግሞ ሥራዋን ለመስራት ወሰነች። ‹‹ዱዋላ ሌዘር ›› የሚል ስያሜንም ሰጥታዋለች። ቃሉ በደቡቡ የሀገራችን ክፍል የቤንች ቋንቋ ሲሆን፣ ‹‹በልዩነት ውስጥ አንድነት›› የሚል ትርጉም እንዳለው ታስረዳለች።

‹‹ዱዋላ ሌዘር›› የተሰኘ ከቆዳ የሚሰሩ የተለያዩ ቦርሳዎችን በሰዎች፣ በደንበኞቿ ምርጫና ፍላጎት ማለትም ‹‹custom made›› ትሰራለች። በተጨማሪም ሰዎች ተጠቅመውባቸው ያረጁ፣ አገልግሎት መስጠት ያቆሙ ቦርሳዎችን በተለየ መንገድ በማደስ በድጋሚ አገልግሎት እንዲሰጡ ታደርጋለች።

ከቆዳ የሚሰሩ ቦርሳዎችን የሰዎችን ምርጫ ተከትሎ በትእዛዝ መስራት በኢትዮጵያ ብዙም አልተለመደም። በመሆኑም በሰዎች ዘንድ ያለው ተቀባይነት ጥሩ መሆኑን ትገልጻለች።

‹‹ስጀምረው ሰዎችን ማሳመን እና ደንበኛ ማግኘት በጣም ከባድ ነበር። በሂደት ግን የተለያዩ ቦርሳዎችን ለመስራት ችያለሁ።›› በማለት ገልጻ፤ ሥራዋን በጀመረችበት ወቅት የቅርቧ የምትላቸው ሰዎች እና ቤተሰቦቿ ሥራዋን ለማበረታት እንድትሰራላቸው ያደርጉ እንደነበር አስታውሳለች።

ሰዎች በፎቶ አይተው የወደዱትን ማንኛውንም እቃ በአካል ሲመለከቱት የሚኖራቸው ምላሽ ተመሳሳይ አይሆንም። ታዲያ እዚሁ በሀገር ውስጥ በፎቶ ያዩትን ልክ ሆኖ ሲያገኙት በእርግጥም በሀገር ውስጥ የተሰራ መሆኑን እንደሚጠራጠሩ ረድኤት ገጠመኟን ታስታውሳለች።

ከቆዳ የሚሰሩ ቦርሳዎችን በማዘጋጀት ሒደት ውስጥ ዋና ግብዓቱ የሆነው ያለቀለት ቆዳ እና ቦርሳ ለመስራት የሚፈልጉ ዚፕ፣ ማንጠልጠያ፣ ቁልፎች እና ማስዋቢያ ጌጣጌጦች በአብዛኛው ከሀገር ውጭ የሚመጡ ናቸው።

‹‹ግብዓቶቹን ማግኘት በጣም ከባድ ነው። ምክንያቱም እኔ የምሰራው ሰዎች ያዘዙትን ቦርሳ በሚፈልጉት የቆዳ ቀለም አይነት ነው። በማላገኝበት ጊዜ ደንበኞቼን ሌላ አማራጭ እንዳለ እነግራቸዋለሁ። ማስዋቢያ እና ጌጣጌጦችም ከውጭ ስለሚመጡ ዋጋቸው ውድ ነው ።›› ስትል ትገልጽና እነዚህም በሥራዋ የምታስተናግዳቸው ችግሮች መሆናቸውን ታብራራለች። በተጨማሪም ረድኤት፣ አነስተኛ የሆነ በራሷ የምታንቀሳቅሰው ቢዝነስ በመሆኑ የምትጠቀማቸውን ግብዓት የምትገዛው በአነስተኛ መጠን ከሚያቀርቡ አከፋፋዮች ነው። እነዚህን በገበያው ውስጥ ለማግኘት አስቸጋሪ የሆኑ ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ የማምረት ሥራ ለመስራት የሚያስችሉ ጥሩ ባለሙያዎች መኖራቸውንም ረድኤት ትገልጻለች።

‹‹ብዙ ሰዎች ደውለውልኝ ግን በትክክል ይመጣል ብለው ይጠይቁኛል። እኔ ግን በቆዳ ላይ ከመስራቴ በፊት በሴንቴቲክ ላይ ትክክለኛውን ለማምጣት በተደጋጋሚ እሞክረዋል። ሰርቼ ስጨርስ ካልወደዱት ደግሞ መልሼ አስተካክለዋለው ።›› በማለት ትገልጻለች።

‹‹ደንበኞቼ መጀመሪያ የሚፈልጉትን አይነት ቦርሳ ዲዛይን ፎቶ ይልኩልኛል። እኔም ለቦርሳው የሚሆነውን የቆዳ አይነት አማራጭ አሳያቸዋለሁ። ከመረጡ በኋላ የሚያስፈልጉኝን እቃዎች አሟልቼ ወደ ሥራ ገባለሁ። ›› የምትለው ረድኤት፣ ተሰርቶ እስኪጠናቀቅም ከ10 እስከ 15 ቀን ጊዜ እንደሚወስድ ገልጻለች።

ረድኤት ሥራዎቿን በአካባቢዋ ለምታውቃቸው ሰዎች በመስራት እና በማስተዋወቅ የምትሰራ ሲሆን፣ በቅርቡ የራሷን ማኅበራዊ ትስስር ገጽ ከፍታ የምትሰራቸውን ሥራዎች በማስተዋወቅ ጥሩ ደንበኞችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ማግኘት ችላለች። የሌሎች ደንበኞቿን ፍላጎት ወደ ሥራ ከምትቀይራቸው ቦርሳዎች ባሻገር አሁን ላይ የራሷን የቦርሳ ዲዛይኖች በማስተዋወቅ ላይ ትገኛለች።

ለዚህም ፈጣሪዋን እና በሥራዋ የደገፏትን ወላጆቿን ታመሰግናለች። በቅርቡም አንድ መድረክ ላይ የራሷን ዲዛይኖች ይዛ እንደምትቀርብ ትገልጻለች። ‹‹ዱዋላ ሌዘር ከተመሰረተ ሁለት ዓመት አስቆጥሯል። ሰዎች ዘንድ ያለው ተቀባይነትም ጥሩ ነው።›› ትላለች።

ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚያስገባትን የሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት በመጠባበቅ ላይ ሆና የፈጠረችው ቢዝነስ አሁን ላይ ደንበኞችን ከማፍራት ባለፈ በተለያዩ ትልልቅ መድረኮች ላይ የራሷን ዲዛይኖች ይዛ እንድትቀርብ አስችሏታል። ወደፊትም ለማሳካት የምታቅዳቸው ሕልሞች አሏት።

‹‹የወደፊት እቅዴ በሀገራችን ውስጥ ብዙም ትኩረት ያልተደረገባቸውን ሰፌድን እና ቆዳን አንድ ላይ በማድረግ፣ የሀገራችን ልዩ ልዩ ጥለቶችን በመጠቀም፣ ከቀርከሀ የሚሰሩ ቦርሳዎችን ለመስራት አስባለሁ።›› የምትለው ረድኤት፣ የተለያዩ ቦርሳን የሚያስውቡ ጌጣጌጦች ከውጭ የሚመጡ እና ውድ በመሆናቸው እዚሁ በሀገር ውስጥ የሚሰሩ ጎበዝ ባለሙያዎች ጋር መስራት ሌላኛው ሀሳቧ ነው።

ወጣቷ ዲዛይነር ረድኤት፣ በቅርቡም ልክ እንደቦርሳው በሰዎች ምርጫ ላይ ያተኮሩ ከቆዳ የሚሰሩ ጫማዎችን መስራት እንደምትጀምር ገልጻለች።

**ይህንን ክፍተት የተረዳችው ረድኤት የተለያየ ዲዛይን ያላቸውን ቦርሳዎች በሰዎች ፍላጎት ላይ ተመስርታ በመስራት ስራዋን ለመጀመር ወሰነች**

# አበረታች ለውጦች የታዩበት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የወርቅ ምርት

ወርቅነሽ ደምሰው

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በወርቅ ማዕድን ሀብትና ምርት ከሚታወቁ የአገሪቷ ክልሎች ተጠቃሹ ነው። ክልሉ በወርቅ ክምችቱና ምርቱ የታወቀ ይሁን እንጂ፣ የወርቅ ሀብቱን በአግባቡ አልምቶ ጥቅም ላይ ማዋል ግን አልተቻለም። ከኋላቀር የወርቅ አመራረት ጋር በተያያዘ የወርቅ ማዕድኑ በሚፈለገው መጠን እንዲለማ አልተደረገም፤ በሕገወጥና የኮንትሮባንድ ንግድ ሳቢያ የሚመረተው ወርቅም ቢሆን ለብሔራዊ ባንክ እንዲገባ እየተደረገ አይደለም። በዚህ የተነሳም አልሚዎቹም፣ ክልሉም አገሪቷም የሚገባቸውን ጥቅም ማግኘት ስላለመቻላቸው ሁሌም ይገለጻል።

ይህ በወርቅ ላይ ሲስተዋል የቆየው ሕገወጥነትና የኮንትሮባንድ ንግድ በዚህ ክልል ብቻ የተወሰነ እንዳልሆነ ይታወቃል። እንደ ሀገር ያለ ችግር እንደ መሆኑ ሀገሪቱ ከወርቅ ማግኘት የሚገባትን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንዳታገኝና ተጠቃሚ እንዳትሆን ተደርጋለች።

መንግሥትም ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ለውጥ ሊያመጡ የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎች ሲሰራ ቆይቷል። ከእነዚህ መካከል አንዱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ወደ ሙሉ ትግበራ መግባትና ብሔራዊ ባንክ ያወጣው የውጭ ምንዛሬ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ ይጠቀሳሉ።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በማዕድናት ምርታማነት በተለይ በወርቅ ምርት ምርታማነትና አቅርቦት ላይ ለውጦች እያመጣ ነው። በአነስተኛ ደረጃ የሚመረተውን የማዕድን ምርት በከፍተኛ መጠን እያሳደገው ይገኛል። በተለይም የወርቅ ምርታማነትና ለብሔራዊ ባንክ እየቀረበ ያለበት ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ማደግ ችሏል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ትግበራ በኋላ በወርቅ ምርት ኤክስፖርት ከፍተኛ ውጤት ተመዝግቧል። በውጭ ምንዛሬ ማስገኘት በኩል በተለይ ቡናና ወርቅ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው።

በሩብ ዓመቱ ለውጭ ገበያ የቀረበው ወርቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቡና በላይ ትልቁን ድርሻ የያዘበት ሁኔታ መፈጠሩም ተጠቅሷል። ለብሔራዊ ባንክ እየቀረበ ካለው ወርቅ ምን ያህል ወርቅ ሲዘረፍ እንደ ነበረ መረዳት እንደሚቻል ገልጸው፣ አምስት መቶ ሚሊዮን ዶላር ገደማ ወርቅ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ማግኘት መቻሉን አስታውቀዋል።

የወርቅ ምርት ሲዘርፉባቸው ከቆዩ አካባቢዎች ጥቂቶቹ ምላሽ እያመጡ ነው። ገና ብዙ ለውጥ ይመጣል። የምንበዘበዝባቸው ብዙ ቀዳዳዎች አሉ። ከእነሱ ውስጥ አንዱ የሆነው ወርቅ መልስ እየሰጠ ይገኛል። ወርቅ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ትልቁን ድርሻ ይዟል ሲሉ አብራርተዋል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የወርቅ ምርት ላይ ለውጥ እንዲታይ ማድረግ መጀመሩን የክልሉ ማዕድን ቢሮ አመልክቷል፤ የክልሉ የማዕድን ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ሞርካ ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ ምርት እየጨመረ መምጣቱን አስታውቀዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ባለፈው በጀት ዓመት ከክልሉ ወደ ብሔራዊ ባንክ የገባው የወርቅ መጠን 274 ኪሎ ግራም ነበር። በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ወደ ባንኩ የገባው ግን 548 ኪሎ ግራም ወርቅ ነው።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ክልሉ በ2017 በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፍ በርካታ ሥራዎች ለመስራት ታቅደው እየተሰሩ ናቸው። ይህን ተከትሎም በወርቅ ምርት ከባለፈው ዓመት በተሻለ ሁኔታ አበረታች ለውጥ ታይቷል።

በተያዘው በጀት ዓመት በመጀመሪያ ሩብ ዓመት 413 ኪሎ ግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ለማስገባት ታቅዶ ነው 548 ኪሎ ግራም ወርቅ ማስገባት የተቻለው። ይህም አፈጻጸሙን ከእቅዱ በላይ እንዲሆን አድርጎታል።



አፈጻጸሙ ከእቅዱ በላይ ብቻ ሳይሆን ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅትም በእጅጉ የላቀ ወርቅ ማስገባት የተቻለበት ነው። ባለፈው በጀት ዓመት ከተገኘው 274 ኪሎ ግራም ወርቅ አኳያም ሲታይ የሩብ ዓመቱ አፈጻጸም በእጥፍ ብልጫ ያለው ነው።

በክልሉ የወርቅ ምርት ላይ ለውጥ ለመምጣቱ ዋንኛው ምክንያት ተደርገው ከሚጠቀሱት መካከል አንዱ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ነው የሚሉት አቶ አድማሱ፤ ማሻሻያው ከተደረገ ጀምሮ በክልሉ የወርቅ ምርት እየጨመረ መጥቷል ይላሉ። በዚህም ምክንያት ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው የወርቅ መጠንም እየጨመረ መሆኑን ይገልጻሉ። በተለይ ብሔራዊ ባንክ ከወርቅ አዘዋዋሪዎች ወርቅ በሚገዛበት ዋጋ ላይ ማስተካከያ ካደረገ በኋላ የወርቅ ምርት በሕጋዊ መንገድ ወደ ብሔራዊ ባንክ እየገባ መሆኑንም አስረድተዋል።

በተጨማሪም በክልሉ የወርቅ ምርትና ግብይት ላይ የሚፈጸመውን ሕገወጥ እና የኮንትሮባንድ ንግድ ለመከላከል ግብረ ኃይል ተቋቁሞ የክትትልና የቁጥጥር ሥራዎችን ሲሰራ መቆየቱም ሌላው ለወርቅ ምርት መጨመር ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል።

የክልሉ ስምንት ወረዳዎች የወርቅ ማዕድን ክምችት እንዳላቸው እንደሚታወቁ ጠቅሰው፣ ከእነዚህም መካከል በአሶሳ ዞን፣ ከማሼ እና በመተከል ዞን ባሉ ወረዳዎች በወርቅ አምራችነት እንደሚጠቀሱ ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በክልሉ 421 ባሕላዊና ልዩ አነስተኛ ማኅበራት ወርቅ የማምረትና የማዘዋወር ፍቃድ ወስደዋል። በክልሉ በሩብ ዓመቱ ከክረምት ወቅትና በአጎራባች አካባቢዎች ካለው የጸጥታ ችግር ጋር በተያያዘ ያቀዱትን ያህል ያልፈጸሙ አምራቾች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በከፍተኛ ደረጃ ወርቅ የማምረት ፍቃድ ያለው ሲሆን፣ ይህ አምራች በሩብ ዓመቱ ለማምረት ካቀደው 13 ኪሎ ግራም የወርቅ ምርት፣ ሁለት ኪሎ ግራም ብቻ ማምረቱን ጠቅሰዋል።

ይህን ከፍተኛ ደረጃ ወርቅ አምራች በሩብ ዓመቱ የነበረው የዝናቡ ወቅት በሚፈለገው መጠን ወደ ማምረት ስራ እንዳይገባ ያደረገው መሆኑን ተከትሎ እቅዱን ማሳካት እንዳልቻለ የቢሮ ኃላፊው አስታውቀዋል። በቀሪዎቹ ጊዜያት ወደ ምርት በመግባት የተሻለ ለማምረት እየሰራ መሆኑን ይገልጻሉ። በሩብ ዓመቱ አብዛኛው የወርቅ ምርት የተገኘው ከባሕላዊና ከልዩ አነስተኛ ወርቅ አምራች ማኅበራት እንደሆነ አመላክተዋል።

በተለይ ወርቅ ለሕገወጥነት የተጋለጠ በመሆኑ በሕገወጦች ሲፈተን ቆይቷል ያሉት ኃላፊው፣ ቀደም ሲል የነበረው የወርቅ መሸጫ ዋጋ ሰፊ ልዩነት ሕገወጥነት እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኖ እንደነበር ጠቅሰዋል። አሁን ብሔራዊ ባንክ ባደረገው የዋጋ ማስተካከያ የተነሳ ዋጋው መንግሥት እየተቆጣጠረው ነው ለማለት የሚያስችሉ ሁኔታዎች መኖራቸውን ይገልጻሉ። እርምጃው የወርቅ ምርት በአግባቡ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲገባ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ውጤቶች እንዲመዘገቡ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ አድማሱ በክልሉ ወርቅ ለማምረትም ሆነ ለማዘዋወር ፍቃድ የሚወስዱ አካላት ሊከተሉ

**ገና ብዙ ለውጥ ይመጣል:: የምንበዘበዝባቸው ብዙ ቀዳዳዎች አሉ:: ከእነሱ ውስጥ አንዱ የሆነው ወርቅ መልስ እየሰጠ ይገኛል**

የሚገባቸውን አሰራር እንዳለም አስታውቀዋል። እነዚህን አሰራሮች ተግባራዊ ማድረግ ላይ ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ ይጠቅሳሉ። በተለይ የአካባቢ ጥበቃ መመሪያዎች ጠብቆ በመስራት ረገድ ክፍተቶች እንዳሉ ተናግረው፣ ለወርቅ ፍለጋ ተብለው የሚቆፈሩ ቦታዎችን አፈር ሳይመልሱ መተው ትልቅ ችግር መሆኑን ጠቁመዋል።

የማዕድን ቁፋሮ በሚካሄድባቸው ቦታዎች ሊፈጠር በሚችለው ጥልቀት የተነሳ የላይኛዋ፣ የመካከለኛው እንዲሁም የታችኛው የአፈር ክፍሎች መንካታቸው እንደማይቀር ጠቅሰው፣ በዚህ የተነሳም በአካባቢና በሰው ላይ አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል አመላክተዋል። ይህንን ችግር ለመቅረፍም በተለያዩ ጊዜያት ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎች ሲሰሩ መቆየታቸው አስረድተዋል።

ከወርቅ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላኛው ተግዳሮት የወርቅ አምራቾችም ሆኑ አዘዋዋሪዎች የሚያደርጉት ሕገወጥ የወርቅ ዝውውር መሆኑን አመልክተው፣ በዚህ የተነሳም ምርታቸውን በሙሉ ወደ ብሔራዊ ባንክ በማስገባት በኩል ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ ይጠቁማሉ። እነዚህን ክፍተቶች በመድፈን ችግሮችን ለመቅረፍም በክልሉ ከተቋቋመው ግብረ ኃይል ጋር በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ እነዚህን ሥራዎች በመገምገም፣ ቁጥጥርና ክትትል የማድረጉ ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መደረጉን ይገልጻሉ።

በተለይ በዘርፉ በተሰማሩ ሕገወጦች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እንደሚደረግ ጠቅሰው፤ በተለይ ወርቅ ከመቆፈር አንስቶ በሚካሄዱ ሥራዎች ላይ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል ብለዋል። ወርቁ በትክክል ተመርቶና በአግባቡ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲገባ ለማድረግ የሚያስችል አቅጣጫ ተይዞ እየተሰራ መሆኑንም አስታውቀዋል። የባሕላዊና ልዩ አነስተኛ የወርቅ አምራቾች ወርቅ ከመቆፈር ጀምሮ እስከ ማምረት መከተል ያለባቸውን አሰራር አስመልክቶ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎችን በመስራት መግባባት ላይ እየተደረሰ መሆኑንም ገልጸዋል።

በክልሉ ባለፉት ይጥል ከነበረው ዝናብ ጋር በተያያዘ ለባሕላዊና ልዩ አነስተኛ የወርቅ አምራቾች ወርቅ የሚያወጡበት ቦታ ድረስ በመሄድ ድጋፍ ለማድረግ ሳይቻል መቆየቱን ጠቅሰው፣ በቀጣይ ጊዜያት ሙያዊ ድጋፎችና የተለያዩ ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች በመስጠት ድጋፍ እንደሚደረግ አመላክተዋል። በተለይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት ከማዕድን ዘርፉ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር እየተሰራ መሆኑን አብራርተዋል።

በክልሉ በየዓመቱ የማዕድን አለኝታ ቦታ እና የማዕድን ልየታ ጥናት እንደሚካሄድ የቢሮ ኃላፊው ጠቁመው፤ በተያዘው በጀት ዓመት ይህንኑ ለማከናወን ታቅዶ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ክልሉ ከወርቅ በተጨማሪ ሌሎች ብዙ አይነት የማዕድናት ሀብቶች እንዳሉና በሁሉም ማዕድናት ላይ እየተሰራ መሆኑን አስታውቀዋል። በተለይ የድንጋይ ከሰልና እምነበረድ ለማምረት ፈቃድ ወስደው ወደ ሥራ የገቡ አምራቾች እንዳሉም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የድንጋይ ከሰል ለማምረት 159 አምራቾች የምርት እና የምርመራ ፍቃድ ወስደዋል። በጸጥታና ከአለመረጋጋት ጋር በተያያዘ አሁን ሥራ ላይ ያሉት ውስን አምራቾች ናቸው። እምነ በረድ ላይም እንዲሁ 258 አምራቾች የምርትና የምርመራ ፍቃድ ወስደዋል፤ ከእነዚህም መካከል በሥራ ላይ ያሉት ውስን ናቸው። በቀጣይም ወደ ሥራ ያልገቡት ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግ ይሰራል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ፤ በክልሉ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት 15ሺ ቶን የድንጋይ ከሰል ለማምረት ታቅዶ፤ ከ27ሺ ቶን በላይ ማምረት ተችሏል። በእምነበረድም በሩብ ዓመቱ 600 ሜትር ኪዩብ ለማምረት ታቅዶ ፤ 459 በላይ ሜትር ኪዩብ ተመርቷል።

በሩብ ዓመቱ የተፈለገውን ያህል ለመስራት የተለያዩ ተግዳሮቶች አጋጥመው እንደነበር ጠቅሰው፤ በአጎራባች ክልሎች አካባቢዎች ባለው የጸጥታና የአለመረጋገት ችግሮች ምክንያት የመንገድ መዘጋቱ እና የመሳሰሉ ችግሮች ማጋጠማቸው በማዕድን ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት የሚፈልጉትን ግብዓት እንዳያስመጡ ተግዳሮት እንደሆነባቸው አመላክተዋል። እንዲያም ሆኖ የተሻሉ ሥራዎች መስራታቸውን ነው ኃላፊው የጠቀሱት።

የማዕድን ዘርፉ ተግዳሮት ሆኖ የቆየው የጸጥታና አለመረጋገት ችግር አሁን እየተፈታ መሆኑን ጠቅሰው፣ በቀጣይም በዘርፉ በሚፈለገው ልክ እንዲሰራ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የማዕድን ዘርፍ ለበርካታ ዜጎች ሰፊ የስራ እድል እንደሚፈጥር ይታወቃል የሚሉት ኃላፊው፤ በክልሉ በሩብ ዓመቱ ከታቀደው አንጻር 80 በመቶ ለሚሆኑ ሥራ አጥ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር እንደተቻለ አመላክተዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ኮከብ ቆጣሪው

ሀብታሙ ባንታየሁ

ወፎች በዝማሬ ንጋቱን ሲያበስሩ ሞባይሌ ደወለ።

አስደግመሽብኝ አለቃ ፈንቴን፣

ሳር ቅጠሉ ሁሉ መሰለኝ አንችን።

ተብሎ የተዘፈነላቸው ጎበዝ መዳፍ አንባቢ ናቸው፤ ሲለግሙ አይጣል ነው።

በመጀመሪያው ትውውቃችን ኮከቤን ቆጥረው መጽሐፍ ገለጡና "ረቡዕ፣ አርብ፣ እሁድ አይሆንህም፤ ጠይም ሴት ክፍልህ ናት" ሲሉኝ ለኑሮስ የትኛው አየር ንብረት ይሆነኛል? ብዬ ብጠይቃቸው "እሱን ሜትሮሎጂ ጠይቅ" ያሉኝ አይረሳኝም።

በሸቦ አልባው ስልክ የሚያነጋግሩኝ አለቃ ፈንቴ ናቸው፤ ሰላምታ እንደተለዋወጥን "እህል ሳትቀምስ በአስቸኳይ ወደ መርጦ ለማርያም አቅና፤ የቀረህ እንደሆነ ተደግሶልሃል" ሲሉኝ በፍርሀት እየተርበተበትኩ ምን? ብላቸው መልስ ሳይሰጡኝ ጠረቀሙት።

መጽሐፍ ገላጩ ሁሉ በየ ነገሩ ለምን እንደሚያስደነብሩኝ አይገባኝም።

ሞትን እንደምፈራ አውቀውብኝ ይሆን? ምን አይነት ጣጣነው።

እህል ሳትቀምስ ከቤት አትውጣ፣ ፀሀይ ሳይወጣ የታመመ ሰው አትጠይቅ፣ መንገድም አትሂድ ያሉኝን አልጣስኩም፤ እስካሁንም እያከበርኩት እገኛለሁ።

ረቡዕ፣ አርብ፣ እሁድ ቀናት እንደማይከፍሉኝ እያወቁ ምን አጠራራቸው? ቀርቼ ምን እንደደገሱልኝ ለማየት ብጓጓም ፈረንጅ የሐበሻን እግር ሲያጥብ ካላየሁ መሞት አልፈልግምና ከመኝታዬ ተነሳሁ።

እጅ መንሻ እንዲሆነኝ አረቄዬን አሸንቅሬ የመርጦለ ማርያምን መኪና ያዝሁ።

ጉዞውም ተጓዡም ተባብረው ድብርት ለቀቁብኝ፤ የጓዳ ችግሮቻቸውን ሰው ይሰማናል ሳይሉ ይዘረግፋሉ፤ አቦ የአዲስ አበባ ሰው ይምጣብኝ እንጂ በየንግዱና በየትራንስፖርት አገልግሎቱ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን ሲጨዋወት እያልኩ ልዩነታቸውን አምሰለሰልሁ።

የአዲስ አበባ ሴት ባሏን በሺህና በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ለኢንቨስትመንት ስትጠይቅ የክልል ሴት ደግሞ ለዕድር ሁለት ብር ትጠይቃለች፤ የአዲስ አበባ ወጣት ሲኒማ ቤት የክልል ወጣት ጠላ ቤት ይውላሉ፣ የአዲስ አበባ ህጻን ልጅ ሲያለቅስ በኬክ ሲያባብል፣ የክልል ህጻን ልጅ ሲያለቅስ ደግሞ በኩርኩም ዝም ይሰኛል።

"ትኬት መልሱ" በሚለው የረዳቱ ትእዛዝ መርጦ ለማርያም መድረሳችንን አወኩኝ።

አለቃ ፈንቴ ተቀብለው ወደ ቤታቸው ወሰዱኝና ጊዜ ደራሹ ላይ ያሰናዱትን የኮቸሮ ግሸር አብረን በላን።

"ቀትሩ ይለፍና አንድ ቦታ አስጎበኝሃለሁ" አሉና ስብሐት አድርሰው ገበታውን ካነሱ በኋላ ያመጣሁትን አረቄ በፍንጃል ቀዱልኝ።

አልጠጣም ብላቸው "ይጎንጥሀል" አሉኝ።

እንግዳ ነገር ሆኖብኝ እንዲያብራሩልኝ ጠየኳቸው።

"ማንኛውም የሚበላና የሚጠጣ ነገር ሁሉ ከሸተተህ ብትወድም ባትወድም መቅመስ አለብህ፤ አለበለዚያ ባንተ ተመስሎ ለመቋደስ የሚቅበዘበዘው ቁሪ ሲቀርበት ይደቃሀል" ብለው ሲያስረዱኝ በድንጋጤ የቀዱልኝን አረቄ በአንድ ትንፋሽ ጨለጥሁት።

"ፉት ካልከው ከዚህም በኋላ እንድትጠጣ አትገደድም፤ ያን ያህል ቢሆንም የእህል ደም ነው አጣጥመው" አሉና አሰር ውሃ በሸክና አስያዙኝ።

እሳቸው አረቄያቸውን እኔ ጠላዬን እየተጎነጨን ስራ እንዴት ነው? ስል የጨዋታችንን ሀረግ መዘዝኩ።

"ምቀኛ እስካለ ድረስ በሽበሽ ነው ስራ አንፈታም" አሉ እየፈገጉ።

በጥያቄ አስተያየት ተመለከትኳቸው፤ የጀመሩትን አረቄ ከልብሰው ሌላ ቀዱና "ምን መሰለህ ገብረ ኪዳን" አሉ እየተመቻቹ።

"ይሄ ህዝብ እገሌ በትምህርት ቀደመኝ፣ እንትና በሀብት በለጠኝ፣ ማንትስ ውርስ ሊካፈለኝ ነውና ከቻልክ ሞቱን ካልሆነ ጉዳቱን አሳየኝ ይልሃል እንጂ ዝናብ ቀረብን፣ እህላችንን አውሬና ተባይ ፈጀብን ያዝልን አይልህም።

ባለው ነገር ፈጣሪውን አመስግኖ እንደመኖር ባንዱ ጸጋ ሌላው ደስ ሊለው ሲገባ ያንተ ማግኘት ያበግነውና በደረቅ ሌሊት ደጃፍህ ላይ የአይጥ አንጀት፣ የተቆረጠ የዶሮ አንገት ይጥልብሃል።

ጠዋት በርህን ስትከፍት ታየዋለህ፤ ከድንጋጤ ጋር ጋኔን ተደርቦ ይደቃህና ለከፋ ስቃይ ይዳርግሃል።

ከቻለም እድሜህን ያሳጥረዋል።

የኋላውን አስበን እኛ እንኳን እምቢ ብንልም ምቀኛ ሁሉ አሞሌ ጨው እያላሰ አዲስ ከብት እንደሚያላምድ ረብጣ ገንዘብ እያሳየ እንክ እንክ ይለናል።

አንዴ ምን ሆነ መሰለህ ... ድጋሙን ገና እንደለመድኩት ባንተ እድሜ ያለ አንድ ወጣት ላይ ስራዬን ፈተንኩት፤ ቃሌ አይስትም ሄዶ ቀጭ ነው።

ይህ ወጣት መስተፋቅር እንድሰራለት ወተወተኝ፤ እግዚአብሔር አልተለየኝም ነበርና የፈተንኩትን ስራዬን እንዳልሰጠው ፈራሁ፤ እንዳልተወው ደግሞ ገበያ ሊዘጋብኝ ሆነ።

ቢጨንቀኝ በብራናው ላይ ብትወድህ ባትወድህ እኔ ምን አገባኝ ብዬ ከተብኩና ባንገቱ እንዲያጠልቀው አዝዤ ሸኘሁት።

አየህ ምቀኛ ሁሉ የሚደረግለትንም ሆነ የሚደረግበትን አያውቅም።

ደመ ነፍሱን ይነዳል ብለው ረዥም ንግግራቸውን እየቋጩ እጃቸውን ወደ መለኪያቸው ሰደዱ።

እኔም ሸክናዬን እየሞላሁ ስፈራ ስቸር አለቃ ፈቃድዎ ከሆነ ያለዎትን ጥበብ ቢያወርሱኝ? ስል ተማጸንኳቸው።

ምን ያደርግልሃል? አሉ የጋቢያቸውን ጎልፋ እያፍተለተሉ።

አሳማኝ ያልኩትን ምክንያት ሁሉ ደረደርኩ።

ስለ ኢትዮጵያ ክፉ የሚያወሩ ሰዎችን ልሳናቸውን እዘጋዋለሁ፣ በመሣሪያና በሠራዊት ብዛት የሚታበዩትን የትኛውንም መንግሥታት በቃላት ብቻ አንኮታኩታቸዋለሁ፣ ሆደ ሰፊው ህዝቤ ላይ እጁን የሚያነሳውን ምቀኛ ሁሉ በረዶ አዘንብበታለሁ፣ የዓባይን ውሀሃ አቁሜ የግብጻውያንን ትዕቢት አስተነፍሰዋለሁ፣ ብሔርን ከብሔር እያጋጩ ጥቅማቸውን የሚያጋብሱና ስማቸውን በቅጡ የማይጽፉ ነገር ግን በፎርጅድ የትምህርት ካርድ ስልጣን ጨብጠው የሀገርን አንጡር ሀብት የሚመጠምጡ ሰዎችን ከኢዮብ በባሰ ቁስል አነዳቸዋለሁ።

ብቻ እርስዎ ያስተምሩኝ ስል ዳግም ለመንኳቸው።

አበክረው ከንፈር መጠጡ።

የሚሰጡኝ መልስ ታውቆኝ ፊታቸውን ላለማየት አቀረቀርኩ።

"አንደኛ ጴጥሮስ ምእራፍ 2÷21 መከራን ስትቀበሉ ታገሱ የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌነት ትቶላችሁ መከራን ተቀብሏል በማለት እንደተናገረው ሀገርህ በሰማይ ከሆነ የምድርን ተድላ ለምን ትሻለህ? በከንቱ የዓለም ፖለቲካ ነፍስህን ከምታቆረፍዳት የማያልፈውን የክርስቶስን ቃል ብትመገባት አይበጅህም? ደግሞም ያጋጠመህን ችግር የምትሻገረው በስሜት ሳይሆን በሰከነ አስተሳሰብ ስትራመድ ነው" ብለው ዝም አሉ።

እሸም እምቢም ባይሉ ከሃሳባቸው አይሆንም ማለታቸውን ተገንዝቤያለሁ።

ማስተማሩን አያስተምሩኝ እናንተስ ብትሆኑ ባላችሁ እውቀት ሀገራችሁን የመጠበቅ ግዴታ የለባችሁም? ስል የብሽቀት ጥያቄ ሰነዘርኩላቸው።

"ገብረ ኪዳን አስተውል ... የግእዝ ቋንቋን ያጠለሸው ለክፋት አገልግሎት ብቻ ማዋላችን ነበር፤ አሁን ግን ትውልዱን ከዚህ አስተሳሰብ በማውጣት ሁለንተናዊ ጥበባችንን መያዙን ልንገልጥለት ይገባል።

በብራና የተሰነዱ ሀገረሰብ መድኃኒቶችን በሳይንሱ እየታገዝን ጥቅም ላይ እናውላቸዋለን፣ የየደብራቱና የየገዳማቱ ታሪክ እየተጠና ለህዝቡ እንዲደርስ እናደርጋለን።

አንተም የተጠራኸው ለዚሁ አላማ ነው" ብለው የያዙትን መጠጥ አገባደው ቆሙ።

አስቤው የማላውቀውና ያልጠበቅሁት ኃላፊነት በመሆኑ እንደ እርጥብ ቆዳ ከበደኝ።

አለቃ ምን መሰለዎት ብዬ ላስረዳቸው ስንተባተብ ስሜን ጠርተው አናጠቡኝ።

"ገብረ ኪዳን አንተ የምታውቀኝ ሥር ስምስ፣ ቅጠል ስበጥስ ነበር፤ ዛሬ ላይ አዲስ ማንነት ለብሻለሁ።

አባ ኪዳነ ማርያም ብለህ ጥራኝ" አሉና መስቀላቸውን አሳለሙኝ።

የባሰውን እንቆቅልሽ ሆኑብኝ።

"መዘንጋት የሌለብህ ነገር ቢኖር ነብዩ ህዝቄል የፈረሰችውን ያባቱን ርስት እየሩሳሌም ከተማን የገነባት በሃያ አምስት ዓመቱ ነው።

ወጣትነትህን ለሀገርህና ለሃይማኖትህ ድከምበት፤ የማስጎበኝህም ቦታ ካንተ ጋር የተያያዘ ታሪክ አለው" ሲሉኝ ደግሞ ምን? አልኳቸው፤ ግራ መጋባቴ እያየለ።

"ሄደን ብናየው አይሻልም?" አሉና እየመሩኝ ወጡ።

# ዓለም አቀፍ



## "ዶናልድ ትራምፕ የጋዛን ጦርነት ለማስቆም ጥረት ማድረግ ጀመሩ"

ተመራጩ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ከመጪው ጥር 11 ቀን 2017 ዓ.ም ከበዓለ ሲመታቸው በፊት ለጋዛው ጦርነት መፍትሄ ለመስጠት ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ መጀመራቸው ተገልጿል፡፡ የዶናልድ ትራምፕ የመካከለኛው ምሥራቅ መልዕክተኛ የጋዛን የተኩስ አቁም እና የታጋቾችን መልቀቅ ስምምነት ላይ ለመምከር ወደ ኳታር እና እስራኤል መጓዛቸውን ሮይተርስ ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል፡፡

በትራምፕ አስተዳደር የቀጣናው መልዕክተኛነት ስፍራን በይፋ የሚረከቡት ስቲቭ ዊትኮፍ ከእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ እና ከኳታር ጠቅላይ ሚኒስትር ሼክ መሀመድ ቢን አብዱራህማን አልታኒ ጋር ተወያይተዋል ነው የተባለው፡፡ ውይይቱ ኳታር ባለፈው ወር ከጋዛ አደራዳሪነት ራሷን ማግለሏን ካሳወቀች በኋላ ዳግም ወደ ድርድር ሚናው መመለሷን አመላካች መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

የትራምፕ አስተዳደር የመካከለኛው ምሥራቅ መልዕክተኛ ከቀጣናው መሪዎች ጋር በነበራቸው ውይይት ፕሬዚዳንቱ ስልጣን ከያዙ በኋላ ጋዛን እና አካባቢውን ማረጋጋት ላይ እንዲያተኩሩ የተኩስ አቁም ስምምነቱ ከበዓለ ሲመቱ በፊት እንዲፈጸም ተስማምተዋል፡፡ የባይደን አስተዳደር የቀጣናው የትራምፕ መልዕክተኛ ከእስራኤል፣ ኳታር እና ሌሎች የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር እየተወያዩ እንደሚገኙ እውቅናው እንዳለው ገልጾ፤ ጦርነቱን የሚያስቆሙ እና ታጋቾችን የሚያስመልሱ የትኛውንም አሜሪካ መር ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴዎች እደግፋለሁ ብሏል፡፡

ሆኖም ተሰናባቹ እና አዲስ የሚተካው አስተዳደር በተኩስ አቁሙ ዙሪያ በጋራ ለመስራት ያሰቡ አይመስሉም ሲል የዘገበው ሮይተርስ ነው፡፡ የትራምፕን ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ በበጎ እንደሚመለከተው ያስታወቀው ሀማስ በበኩሉ፤ በዘመነ ትራምፕ በሚኖሩ የተኩስ አቁም ስምምነት ሂደቶች ዙሪያ ለመወያየት በቅርቡ አመራሮቹን ወደ ዶሃ እንደሚልክ አስታውቋል፡፡

ትራምፕ ከሰሞኑ "ታጋቾቹ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆኜ ቢሮ ከምገባበት እኤአ ከጥር 20/ 2025 በፊት ካልተለቀቁ በመካከለኛው ምሥራቅ ከባድ ችግር ይፈጠራል ማለታቸውን ጠቅሶ አል ዐይን ዘግቧል፡፡

## በኮንጎ በጉንፋን መሰል አዲስ በሽታ ምክንያት 79 ሰዎች ሞቱ

በዲሞክራቲክ ኮንጎ ሪፐብሊክ የጉንፋን ምልክቶች ባሉት አዲስ በሽታ ምክንያት ቢያንስ 79 ሰዎች መሞታቸውን የሀገሪቱ የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ። የማዕከላዊ አፍሪካዊቷ ሀገር የጤና ሚኒስቴር እንዳለው ከሟቾቹ መካከል አብዛኞቹ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 18 ያሉ ታዳጊዎች መሆናቸው ተገልጿል።

ትኩሳት፣ የራስ ምታት፣ ሳል፣ ለመተንፈስ መቸገር፣ ከአፍንጫ የሚወጣ ፈሳሽ እና የደም ማነስ የበሽታው ምልክቶች ሲሆኑ፣ እስካሁን ከ300 በላይ ሰዎች እነዚህን ምልክቶች ማሳየታቸው ታውቋል። የሕክምና ባለሙያዎች በሽታው በስፋት ታይቶበታል ወደ ተባለው ክዋንጎ ግዛት አምርተው የበሽታውን ባህሪ እና ህመምተኞችን እየመረመሩ ይገኛሉ።

ሴፍሪዬን ማንዛንዛ የተባሉ የሲቪል ማኅበረሰብ መሪ ለሮይተርስ የዜና ወኪል እንደተናገሩት፤ በበሽታው የሚያዙ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄዱ ሁኔታው አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። "ፓንዚ ገጠራማ የጤና ዞን ነው። በዚህ ምክንያት የመድኃኒት አቅርቦት እጥረት አለ" ሲል ግለሰቡ ተናግሯል።

የዓለም ጤና ድርጅት የአፍሪካ ቀጣናዊ ቢሮ ባለሥልጣን "ወደ ሥፍራው አንድ ቡድን ልከን ናሙና ሰብስቦ በቤተ-ሙከራ ምርመራ ለማድረግ አቅደናል" ሲሉ ተናግረዋል። የአካባቢው ባለሥልጣናት ማኅበረሰቡ ሁኔታዎችን በእርጋታ እና በንቃት እንዲጠባበቅ አሳስበዋል።

በሥፍራው የሚገኙ ነዋሪዎች እጃቸውን በሳሙና እንዲታጠቡ፣ በጋር ከመሰባሰብ እንዲቆጠቡ እና የሟቾችን አስከሬን ብቁ ከሆኑ የጤና ባለሙያዎች ፈቃድ ውጪ እንዳይነኩ ማሳሰቢያ ተሰጥቷቸዋል።



የአካባቢው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ከአውሮፓውያኑ ኅዳር 10 እስከ 26 ቀን 2024 ባለው ጊዜ 67 ሰዎች በበሽታው ምክንያት መሞታቸውን ተናግረዋል።

"የፓንዚ ሆስፒታሎች በመድኃኒት እጥረት ሳቢያ ወረርሽኙን ማስቆም አልቻሉም። በፍጥነት እርዳታ ያስፈልገናል" ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። ዲሞክራቲክ ኮንጎ ውስጥ ከዚህ አዲስ ወረርሽኝ በተጨማሪ በኤምፖክስ ወረርሽኝ ምክንያት አደጋ ላይ ወድቃለች። ካለፈው ዓመት ጥር እስከ ሐምሌ ባለው ጊዜ 14 ሺህ 500 ሰዎች በበሽታው ተይዘዋል።

አዳዲስ በሽታዎች በተደጋጋሚ የሚከሰቱባት ዲሞክራቲክ ኮንጎ በኢቦላ ቫይረስ ሳቢያ ላለፉት በርካታ ዓመታት ብዙ ፈተናዎችን አልፋለች ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# 27 ዓመታት ኤች አይቪን በመከላከል ሥራ

**ቤዛ እሸቱ**

ያኔ ከዛሬ 27 ዓመት በፊት በየዕለቱ የእድር ጡሩንባ መስማት አዲስ አልነበረም። በየአካባቢው በርካታ የኤች አይቪ ኤድስ በደማቸው የሚገኝ ወገኖች አሉና። ዛሬ ማን ይሆን ብሎ መቅበር እስኪታክት እድርተኛው ተሰላችቷል። ባስ ሲል በአንድ ቀን ከአንድ በላይ ቀብር ይስተናገዳል። ከሚሞተውም በላይ በርካቶች አልጋ ይዘው አስታማሚ አጥተዋል። በርካታ ህጻናት ወላጅ አልባ ሆነዋል። በርካታ ወላጆች ይጦሩኛል ያሏቸውን ልጆች ተነጥቀው በእድሜቸው መጨረሻ የልጅ ልጅ አሳዳጊ እንዲሆኑ ተገደዋል። ያኔ ነበር የነገሮች አካሄድ ያልጣማቸው ወጣቶች በጋራ ሰብሰብ ብለው ስለጤናቸው ለመመካከር የወሰኑት። ኤች አይቪ ኤድስን ስለመከላከል ለመምከር የተሰባሰቡት።

የወጣቶቹ ስብስብ እራሳቸውንና ሌሎች ወጣቶችን ከኤች አይቪ ኤድስና ተዛማጅ የጤና ችግሮች መከላከልን ያለመ ነው። የዛሬ 27 ዓመት ጅማሬውን ሲያደርግ ሕይወት ጸረ-ኤድስ ማኅበር በኢትዮጵያ ይሰኝ ነበር። ሟቹም ታማሚውም በዝቶ ቢያዩ የበኩላችንን እናድርግ ብለው ተደራጁ። ይሁን እንጂ ስለበሽታው በቂ መረጃ አልነበራቸውም፤ እንዴት ራሳቸውንም ሆነ ሌሎችን እንደሚጠብቁ አያውቁም። ያኔ ከመስራች ወጣቶች መሃል የነበሩትና አሁን የሕይወት ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ ጌታዓለም ካሳ እንደሚያስረዱት፤ በወቅቱ በአካባቢያቸው ይንቀሳቀሱ የነበሩ ድርጅቶችን በመጠጋት ምን መስራት እንዳለባቸው ልምድ ቀሰሙ። ያኔ ከማሰልጠን መሰልጠን ይቀድማልና ሕብረተሰቡን በምን መልኩ ሊያግዙ እንደሚችሉ የሚያሳዩ ሥልጠናዎችን ወሰዱ።

ወጣቶቹ አስፈላጊውን ስንቅ ከሰነቁ በኋላ የኤች አይቪን ስርጭትና በኤድስ ምክንያት የሚሞት ወገናቸውን ቁጥር ለመቀነስ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ተንቀሳቀሱ። በተለይ ለወጣቶች ተስማሚ ናቸው ተብለው በሚታሰቡ የኪነጥበብ መንገዶችን በመጠቀም በስፋት ሰሩ። በድራማዎች፣ በመዝሙር፣ በግጥም፣ በዘፈን፣ በራሪ ወረቀቶችን በመበተን ወጣቱና ሌላው የማኅበረሰብ ክፍል ግንዛቤ እንዲጨብጥ አደረጉ።

ያኔ ኤች አይቪ ኤድስ እንደጭራቅ ይሳል ነበር የሚሉት አቶ ጌታዓለም፤ ሰው ኤች አይቪ አለበት ከተባለ መድሎና መገለሉ ከፍተኛ ስለነበር የመከላከል ሥራቸው ልዩ ትኩረት እንደተሰጠው ያነሳሉ። ቫይረሱ በደማቸው ከሚገኝ ሰዎች ጋር በጋራ መድረክ በማመቻቸት መገለልና መድሎን የሚቀንሱ ትምህርቶችና ስለቫይረሱ የማስተማር ሥራ እያዘናኑና ቁምነገር እያስጨበጡ ይሰሩ እንደነበርም ያስታውሳሉ። ያኔ የነበሩት ወጣቶች የአስተሳሰብ አድማስ እየሰፋ ሲሄድ የወጣቶቹን እንቅስቃሴ ያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች እነሱን ለመደገፍ መነሳሳታቸው የተሻለ ሥራ ለመስራት እንዳስቻላቸውም ይጠቅሳሉ።

ከኤች አይቪ በተጨማሪ የሥነ-ተዋልዶ ጤና፣ ሥርዓተ ጾታ ላይ መስራትና በተለያዩ መድረኮች የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ማስፋት መቻላቸው ከወጣቶች ማሕበርነት ከፍ ያለ ሀገራዊ ሥራ መስራት እንደሚችሉ ተረዱ። አቅማቸውንም አወቁ። በዚህም አስፈላጊውን የምዝገባ ሂደት በማሟላት እ.አ.አ በ2000 ‹‹ሕይወት ኢትዮጵያ›› በሚል ስያሜ ሀገር አቀፍ ግብረሰናይ ድርጅት በመሆን መስራት የሚያስችል ምዝገባና ፈቃድ አገኙ። ከዛ ጊዜ ጀምሮ እንደ አንድ ድርጅት ስትራቴጂክ እቅድ በማውጣት ወደ እንቅስቃሴ ገቡ።

ሕይወት ኢትዮጵያ ጤና ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ከጤናም ኤች አይቪ ኤድስ ዋና የድርጅቱ ትኩረት መሆኑን ይናገራሉ። የወጣቶች ሥነ-ተዋልዶ ጤና ሌላው የድርጅቱ ትኩረት ነው። ወጣቶች ስለ ሥነ-ተዋልዶ ጤና ግንዛቤያቸው ከፍ ሲል ሌላው የኤች አይቪ ኤድስ ስርጭትን ዝቅ ማድረጊያ መንገድ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት ተሰርቷል ይላሉ።

እንደ አቶ ጌታዓለም ማብራሪያ፤ ኤችአይቪ ትልቅ



**የሕይወት ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ ጌታዓለም ካሳ**

ጫና ከሚያደርስባቸው ዘርፎች አንዱ የትምህርት ዘርፍ ነው። ለዚህም በትምህርት ቤት ያሉ አካላት ስለኤች አይቪ ኤድስ በቂ መረጃ እንዲኖራቸውና ቫይረሱን ለመከላከል ግንዛቤ እንዲኖራቸው ተከታታይ የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች ተሰርተዋል። ድርጅቱ በተመሰረተበት ወቅት በኤድስ ምክንያት ወላጆችን በማጣትና መሰል ጫናዎች ምክንያት ትምህርት በተገቢው መልኩ አለመከታተልና ማቋረጥ ያጋጥም ነበር። ድርጅቱ ተማሪዎችን መደገፍ፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ግንዛቤ በመፍጠር፣ ትምህርት ቤቶችን ለተማሪዎች ምቹ በማድረግ ላይ በትኩረት ሰርቷል።

የኤች አይቪ ኤድስ ጉዳይ ከሥርዓተ ጾታ ጋር ይያያዛል የሚሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ የጾታ እኩልነት መከበርን የተቋሙ ትኩረት አድርገው እየሰሩ መሆኑን ጠቅሰዋል። የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን ለማምጣትና ጥቃትን ለመከላከል ዋናው ጥቃት አድራሻ የሆኑት ወንዶች የመፍትሄው አካል መሆን አለባቸው ብለው ያምናሉ፤ ለዛም ይንቀሳቀሳሉ። ሌላው የድርጅቱ ትኩረት የሕጻናትና ወጣቶች መብት መጠበቅ ነው። የሕጻናትና ወጣቶች መብትን ማስከበር እንዲቻልና ሕጻናትና ወጣቶች መብቶቻቸውን እንዲያውቁ የተለያዩ ሥልጠናዎች ይሰጣቸዋል።

ድርጅቱ ከሚሰጠው ሥልጠና በተጨማሪ በሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ መድረኮች ተሳትፈው ልምዶችን እንዲቀስሙና ለአቻዎቻቸው እንዲያካፍሉ ይደረጋል። የሕጻናትና የወጣቶችን መብት ከማክበር አንጻር በሀገሪቱ ሕጎች የተቀመጡና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ማክበር ያስፈልጋል። በመሆኑም ድርጅቱ እየሰራም ይገኛል ብለዋል።

በሀገራችን ድህነት ከባድ ጫና እያሳደረ መሆኑን የሚናገሩት አቶ ጌታዓለም፤ በተለይ ወጣት እናቶች ችግር ላይ ናቸው ይላሉ። በዚህም ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት የማይልኩ፤ መመገብ የማይችሉ፣ የትምህርት ቁሳቁስ ማሟላት የማይችሉ መኖራቸውን ያነሳሉ። ይሄንን ለመፍታት የኢኮኖሚ ድጋፍ ያስፈልጋል። ለዚህም ሥልጠና በማሰልጠንና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ ችግር ላይ ያሉ እናቶች እየሰሩ ልጆቻቸውን መደጎም የሚችሉበት ሁኔታ ይመቻቻል። ይሄ በሌላ መንገድ ከኤች አይቪ ኤድስ ጋር ይያያዛል። ኤች አይቪ በደማቸው የሚገኝ እናቶች የጸረ-ኤች አይቪ መድህኒት ሲወስዱ ተመጣጣኝ ምግብ መመገብ ተመራጭ በመሆኑ የኢኮኖሚ ድጋፍ በድርጅቱ እንደሚደረግም አንስተዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገሪቱ የተነሳውን የእርስ በእርስ ግጭት ተከትሎ ድርጅቱ በሚሰራባቸውና ጦርነቱ ባለባቸው አካባቢዎች ሰዎች እየተፈናቀሉና ለችግር እየተዳረጉ ነው። ጥቃት ስደት ሲኖር ያልተፈለገ የግብረስጋ ግንኙነት ይኖራል። በዚህ የተነሳ የኤች አይቪ ኤድስ ተጋላጭነት ይጨምራል፤ አላስፈላጊ እርግዝናም ሊፈጠር ይችላል። በመሆኑም በዚህና መሰል ችግር ላይ ያለን ማኅበረሰብ መርዳት፤ ከትምህርት የራቁ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት መመለስና ወላጆችና ልጆች ወደቀያቸው እንዲመለሱ መርዳት ድርጅቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጀመረው ፕሮግራም ነው።

ድርጅቱ በሚሰራበት አካባቢ የወደሙ ትምህርት ቤቶች የትኞቹ ናቸው ምን ጎደላቸው? ምን ያህል ተማሪዎች አሉ? ምን ያህሉ ተሰደዱ? ምን ድጋፍ ይሻሉ? የሚለውን በመለየት ድጋፍ ያደርጋልም። ተፈናቃይ ዜጎች ቤታቸውን ጥለው ስለወጡ አልባሳትና መጠለያ ጭምር የላቸውም። ስለዚህ የድርጅቱ ድጋፍ ምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑትን ጭምር እንደሚያካትት ተናግረዋል። ከግለሰቦችም በተጨማሪ ለትምህርት ቤቶች የሚያስፈልጋቸውንና የጎደላቸውን ግብዓት የማሟላት ሥራ መስራታቸውን ጠቅሰው፤ በደብረብርሃን፣ በሸዋሮቢት ጎንደር በሚገኙ መጠለያዎች ቀጥታ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ነገሮችን ያካተተ ድጋፍ መደረጉንም በአብነት አንስተዋል።

እንደ ሕይወት ኢትዮጵያ ሕጻናትና ወጣቶች ናቸው የኛ ትኩረቶች የሚሉት አቶ ጌታዓለም፤ ሕጻናትና ወጣቶች ጤናማ ደስተኛ፤ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ ለማድረግ አስፈላጊውን ሥራዎች እንሰራለን። አለፍ ሲልም የሕጻናትና ወጣቶችን መብት የሚነኩ፣ ጤንነታቸውን የሚጎዳ ማንኛውንም አካል በፕሮግራሙ እንዲሳተፍ እናደርጋለን። ለሕጻናትና ወጣቶች ተስማሚ ሁኔታን መፍጠርና ጤናማ ደስተኛና አምራች ትውልድ ኢትዮጵያ ውስጥ ማየት ራዕያችን በመሆኑ ይህንን በስፋት እንሰራበታለን ሲሉ አስረድተዋል።

ከሕግ አውጪና አስፈጻሚ አካላት፣ ከቤተሰብ ከሚዲያና አጠቃላይ በሕጻናትና ወጣቶች ዙሪያ ካሉ ተቋማትና ማኅበረሰብ ጋር ሥራዎችን በትብብር እንደሚሰሩ የሚገልጹት ሥራ አስፈጻሚው፤ ሕይወት ኢትዮጵያ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ መሆኑን ይገልጻሉ። ምክንያታቸውም ወጣቶች ማኅበራዊ ሚዲያን እንዴት ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ በሚገባ አለማወቃቸው ነው። እናም ‹‹ሚዲያ ስማርት ዩዝ ኔትወርክ›› የሚል ተቋም ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመመስረት እየሰሩ ስለመሆናቸው ይናገራሉ።

ሕጻናትና ወጣቶች ምቹ አካባቢ እንዲኖሩ፤ ጤናማ እንዲሆኑ ይፈልጋል። ከችግር ነጻ የሆነ ኑሮ እንዲኖሩና ተምረው ለሀገር የሚጠቅሙ ዜጎች ሊሆኑ ይገባል። ስለዚህም ያለእድሜያቸው የሚዳሩ ልጆች ቢያንስ ራሳቸው መወሰን እስኪችሉ ድረስ እንዳይዳሩ እንሰራለንም ይላሉ።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ አብዛኛው የድርጅቱ ገቢ ከውጪ በሚገኝ ድጋፍ (ፈንድ) የተገደበ ነበር። አሁን ግን የሀገር ውስጥ ሀብት ማሰባሰብ አስፈላጊነት ታምኖበት የተሻለ የሀገር ውስጥ ሀብት የማሰባሰብ ልምድ ካላቸው ሀገር በቀል ግብረሰናይ ድርጅቶች ልምድ መቅሰም ተጀምሯል። ድርጅቱ የሀገር ውስጥ ሀብት ማሰባሰብ እንዲችል በቅርቡ የሀገር ውስጥ ሪሶርስ ሞብላይዜሽን ቡድን አቋቁሟል። የድርጅቱ መስራቾች የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በመሆን ቀጥለዋል። ከዛ በተጨማሪ ድርጅቱ ውስጥ በተለያየ ጊዜ አገልግለው የተሻለ ሕይወት ፍለጋ በሰላም ከድርጅቱ የለቀቁ አባላት የድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ አባል የሚሆኑበት ሁኔታ ተመቻችቷል። እነዚህ አባላት ከጠቅላላ ጉባኤ አልፈውም እስከቦርድ የሚያገለግሉበት ሁኔታ አለ። ሰዎች የድርጅቱ ባልደረባ እንዲሆኑ ሰልጥነዋል፣ ገንዘብ፣ ጊዜ፣ እውቀት ወጥቶባቸዋል። ምንም እንኳን የተሻለ ነገር ፍለጋ ቢሄዱም በልምዳቸው እንዲያገለግሉ ሁኔታዎች ተመቻችቷል።

በተለያየ ጊዜ ከሀገር ውስጥ በጎ ፈቃደኞች በተጨማሪ ዓለምአቀፍ በጎ ፈቃደኞች ከድርጅቱ ጋር እንደሚሰሩ የሚያነሱት አቶ ጌታዓለም፤ በማኅበረሰቡ ውስጥም ከድርጅቱ ጋር የሚሰሩ የሕጻናት የወጣቶች ክበባትና የማኅበራት አደረጃጀቶች መኖራቸውን በማንሳት የኛ ሥራ ማስተባበር ነው ብለዋል። አብዛኛው ሥራ በበጎ ፈቃደኞች እንደሚሰራም አንስተዋል። ለአብነትም በሰሜን ሸዋ ‹‹ኮሚኒቲ አክሽን ቲም›› ተብሎ የተሰየመ ያለእድሜ ጋብቻን የመከላከል ፕሮግራም መኖሩንና ዋናው ሥራ በእነሱ እንደሚሰራ ገልጸዋል። ከሕግ አካላት፣ ከሀይማኖት አባቶች ከሴቶችና ሕጻናት ቢሮ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ቢሮዎች ጋር በመሆን በየቦታው እንዲህ አይነት አደረጃጀቶችን በመፍጠርም እንደሚሰሩ ተናግረዋል። በእነርሱ በኩል አስፈላጊውን ግብአት በማሟላት ሥልጠና በመስጠትና ቴክኒካል ድጋፍ በማድረግ ሥራው በፈቃደኝነት በማኅበረሰቡ እንዲሰራ እንደሚደረግም ጠቁመዋል።

ሕይወት ኢትዮጵያ የተመሰረተው በበጎ ፈቃደኞች በመሆኑ የበጎ ፈቃድ ሥራን ያበረታታል። ወጣቶች በበጎ ፈቃድ ሥራ እንዲያልፉ ይፈልጋል። ይህ መሆኑ ደግሞ በበጎ አድራጎት ድርጅቱን ከማገልገል ጀምረው ድርጅቱን የተቀላቀሉ ሠራተኞች እንዲኖሩ አስችሏል። ድርጅቱና ሌሎች በሰሩት ሥራ የኤች አይቪ ኤድስ እንቅስቃሴ ላይ ለውጥ መጥቷል ብለው እንደሚያምኑ የሚያነሱት ሥራ አስፈጻሚው፤ ሆኖም ኮቪድ 19 ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ሆኖ በመከሰቱና በሀገራችን ጦርነት መቀስቀሱን ተከትሎ በኤች አይቪ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር እንዳይጨምር ስጋት አላቸው። የዚህ ምክንያቱም የመንግስት፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ የሚዲያና የሌሎች አካላት ዋና ትኩረት ወደ ሰብአዊ ድጋፍ እየዞረ መሄዱ ነው። ስለሆነም የኤች አይቪ ኤድስ ጉዳይ ወደ ኋላ እንዳይቀርና የቀደመው ታሪክ እንዳይደገም ሁሉም ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንደሚገባው አሳስበዋል።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ያልተቀየረ ወገን የማይቀይረው እውነታ!

ዘካርያስ

እንደ ማህበረሰብ ወይም ሀገር በተፈጥሮ አደጋ፣ በጦርነት፣ በወረርሽኝና በመሳሰሉት ሳቢያ ለተወሰነ ጊዜ ለተረጂነት ሊጋለጥ ይችላል:: ይህ ሁኔታ የምልልስ፣ የቆይታ ልዩነት ከሌለ በስተቀር ተፈጥሯዊ ክስተት ነውና እዚህም እዚያም የነበረ፣ ያለ፣ ሊኖር የሚችል ነው::

ይህ በሚያጋጥምበት ጊዜ አደጋውን ሊያደርስ የሚችለውን ቀውስ ለመቆጣጠር በሚደረግ ጥረት ፈተናዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: አደጋ ድንገተኛ ነገር ነውና በእጅ ያለውን እምቅ አቅም ማሰብ ጭምር ሊሳን ይችላል፤ ለክፉ ቀን በሚል የተቀመጠም ቢኖር ላይበቃ ይችላል፤ የተከሰተው አደጋ ነዋ::

ይሄኔ ወዳጅ ሀገሮች ብቻም ሳይሆኑ ጥሪ የተደረገላቸው ሀገሮች፣ ማህበረሰቦች፣ ወዘተ በአስቻጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝን ማህበረሰብ በአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ ለመድረስ ይረባረባሉ፤ አደጋው እንዲሁም አደጋው ሊያደርስ የሚችለው ቀውስ በቁጥጥር ስር ውሎም፣ አልፎም ተርፎ ወደ መደበኛው መስመር መመለስ እስከሚቻል ድረስ የምግብና የመሳሰሉት ድጋፎችን ሲያደርጉም ይስተዋላል::

ሀገራችን በአንዳንድ ክልሎቿ በተደጋጋሚ በተከሰተባት አስከፊ የድርቅ አደጋ ሳቢያ ይህን በሚገባ ታውቀዋለች:: የደርቅ አደጋዎቹ የዜጎችን ህይወት የቀጠፉባቸው፣ አቅማቸውን የሰለቡባቸው፣ አርሶ አደሮች ከብቶቻቸውን ሰብላቸውን አጥተው ቂያቸውን ጥለው እስከመሰደድ የደረሱባቸውም ወቅቶች እንደነበሩ ይታወሳል::

የሀገሪቱ መንግሥታት በአደጋዎቹ ለተጎዱ ወገኖች የአስቸኳይ ጊዜ ሰብአዊ እርዳታ ሲያቀርቡ አስተውለናል:: የ1977ቱን የድርቅ አደጋ ተከትሎ የነበረውን ርብርብ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል:: ግዙፍ የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ተቋቁሞ ለዓመታት ሠርቷል::

ከዚህ በተጓዳኝም ችግሩን ለዘለቄታው ለመቀልበስ የተፈጥሮ ሀብታቸው ከተመናመነባቸውና በድርቅ አደጋ በቀላሉ ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎችን /አርሶ አደሮችን/ ወደ ተለያዩ ለም አካባቢዎች ወስዶ እስከ ማስፈር የደረሰ እርምጃ ወስደዋል:: በወቅቱ ሰፈራው ሌላ ፖለቲካዊ ትርጉም ቢሰጠውም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች በሰፈራው እንዲካተቱ ተደርጓል:: በዚህም ራሳቸውን እስከሚችሉ ድረስ የተለያዩ ድጋፎች እየቀረበላቸው በኖሩበት የግብርና ሥራ እንዲሰማሩ ተደርጓል:: በዚህም በርካታ ሀገሮች፣ ማህበረሰቦች ከእነዚህ ተጎጂዎች ጎን በመቆም አጋርነታቸውን፣ ኃላፊነታቸውን ፣ የወገን አለኝታነታቸውን በተጨባጭ አሳይተዋል::

ሀገሪቱ ድርቁ ያስከተለውን ጉዳት ተከትሎ በዜጎች ላይ የደረሰው አደጋ የበለጠ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ ለማድረግም በገዛ ራሷ ዜጎችና በመንግሥት አቅም ብዙ ጥረት አድርጋለች፤ በወዳጅ ሀገሮች፣ በእርዳታ ሰጪ ተቋማት ድጋፍ ሲደረግላት እንደነበር ይታወቃል:: ይህ ርብርብ ዜጎችን ከከፋ ሞት፣ ጉዳት፣ ሀገርንም ከከፋ ቀውስ መታደግ ችሏል::

ገጽታዋንም በእጅጉ የጎዳባቸውን ጊዜያት ታስታውሳለች:: ይህ ጉዳት ጥሎባት ያለፈውን መጥፎ ጠባሳ መቼም አትረሳውም:: በእነዚህ ክፉ ቀናት ከአጠገቧ ሆነው አለን ያሏትንም አትዘነጋም፤ ሀገሪቱና ሕዝቧ ለእዚህ ታላቅ ውለታም በየወቅቱ በእነዚያ ክፉ ቀናት ከአጠገባቸው ሆነው ድጋፍ ላደረጉላቸው ሁሉ ምስጋናቸውን አቅርበዋል:: ምስጋናውንም ድጋፍ ያደረጉ ሀገሮች ድረስ በመሄድ ጭምር ያቀረቡበት ሁኔታ እንዳለም ይታወቃል::

ድጋፍ ያደረጉ አካላት ፣ የሀገሪቱ መንግሥትና ዜጎች ጥረታቸው እልቂትን፣ ስደትን፣ ወዘተ ከመቀነስ አልፎም ተርፎ ማስቀረት የቻለ ብቻ አይደለም:: ሰፋሪዎቹም ጠንክረው በመስራት የድርቅ አደጋን እንዲበቀሉ አስችሏቸዋል::

ድርቅ እየተመላለሰ እናት አባታቸውን ወንድሞች እህቶቻቸውን ልጆቻቸውን ቢበላባቸውም፣ ለእንግልት ቢዳርግባቸውም፣ ሀብት ንብረታቸውን ቢያሳጣቸውም በተፈጠሩላቸው ምቹ ሁኔታዎች በመጠቀም፣ ጠንክረው በመስራት የምግብ ዋስትናቸውን ከማረጋገጥ አልፈው ለገበያ የሚያመርቱ ወይም ትርፍ አምራች እስከመሆን የደረሱበት ሁኔታም ታይቷል:: በአንዳንድ ክልሎች ከሚገኙ እነዚህ ህብረተሰቦች የሚሰማውም ዜና ይህንን ያረጋገጠ ነው::

መንግሥት የድርቅ አደጋ ከሚመላለስባቸው አካባቢዎች ተጎጂዎችን ወደ ሌላ አካባቢ ወስዶ ከማስፈር ይልቅ ለድርቅ አደጋ ተጋላጭነታቸውን የሚቀንሱ ስትራቴጂዎችን በመንደር በሴፍቲኔት መርሀ ግብር አማካይነት ጥሪት እንዲያፈሩ ለማድረግም ሠርቷል፤ ልማታዊ ሴፍቲኔት በተሰኘው በዚህ መርሀ ግብር አርሶ አደሮች ከመደበኛው የግብርና ስራቸው ጎን ለጎን በእንስሳት እርባታ፣ ንብ ማነብ፣ ሌሎች ስራዎች ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ በማድረግ ድርቅ ቢከሰት በቀላሉ ለጉዳት የማይዳረጉበትን ሁኔታ መፍጠር ተችሏል፤ ድርቅ ኮሽ ባለ ቁጥር ዜጎች ማቄን ጨርቄን ሳይሉ ወደሌላ አካባቢ ይሰደዱ የነበረበትን ሁኔታ ለማስቀረት ተሰርቶ ውጤታማ መሆን ተችሏል::

የድርቅ አደጋን ለመከላከል እነዚህና እነዚህ ላይ ብቻ አይደለም ሲሰራ የቆየው:: ለድርቅ አደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ግድቦችን በመገንባትና ውሃ በማቆር፣ የውሃ ጉድጓዶችን በመቆፈር አርሶ አደሮች የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የሰብል እና የመኖ ልማት በማካሄድ የድርቅ ተጋላጭነታቸውን መቀነስ እየተቻለ ነው::

ዜጎች ድርቅ ሲከሰት አካባቢያቸውን ለቀው የሚሄዱበትን ሁኔታ ማስቀረት እየተቻለ ነው:: ባሉበት ቦታ ድጋፍ በማድረግ ለሚቀጥለው ምርት ዘመን ማዘጋጀት ላይ በትኩረት ይሰራል:: ለዚህ ሁሉ ስራ የተለያዩ አካላት ድጋፍ ስራ ላይ ውሏል:: ድጋፉን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም ተሰርቷል፤ የድርቅ አደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ስራ ውሎም ውጤታማ ተግባር ተከናውኖበታል:: ይህ ሁሉ ግን የድርቅ አደጋ ጉዳት ያደረሰባቸውንና ጉዳት ሊያደርስባቸው የሚችሉትን ለመታደግ የተካሄደ ስራ ነው::

ሀገሪቱ ድርቅ በተደጋጋሚ ያደርስባት የነበረውን ጉዳት ለመቀነስ ስታከናውናቸው ከነበሩ ተግባሮች ጎን ለጎን በግብርና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ላይ አጥብቃ ሰርታለች:: ሀገሪቱ እየጨመረ የሚመጣውን የግብርና ምርቶች ፍላጎት ለማሟላት፣ ለአግሮ ኢንዱስትሪዎች ግብአቶችን በስፋት ለማቅረብ፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየወጣባቸው ወደ ሀገር ውስጥ ይገባ የነበረውን ስንዴ በሀገር ውስጥ የስንዴ ምርት ለመተካት እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ምርቶች ምርታማነት ለመጨመር በትኩረት ሲሰራ ቆይቷል፤ እየተሰራም ይገኛል:: የምግብ ዋስትናንና የምግብ ስርአትን አልፎም ተርፎ የምግብ ሉአላዊነትን ማረጋገጥ የዚህ ዘመን ቁልፍ ተግባር ተደርገው እየተሰራባቸው ናቸው::

በስንዴ ልማት እየተከናወነ ያለው ስኬታማ ተግባር ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳል:: ሀገሪቱ ለስንዴ ልማት የሚሆን ሰፊ ለም መሬት፣ አየር ንብረት፣ ውሃ ሰፊ ጉልበት እያላት ስንዴ ለዚያውም ለተቀረው ልማቷ በእጅጉ የሚያስፈልጋትን የውጭ ምንዛሪ እየገፈገፈች ስትገዛ ኖራለች:: ግዥው የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የተደረገ እንደመሆኑ መደረግ ያለበት ነው::

ሀገሪቱ በአንድ ወቅት በተፈጠረባት ጫና የተነሳ ለዜጎቿ የሚያስፈልገውን ይህን ስንዴ ለመግዛት የውጭ ምንዛሪ መድባ ስንዴ አምራቾች ወይም አቅራቢዎች እንዳይሸጡላት ጫና ተደርጎባቸው እንደነበር ይታወሳል:: ይህ ችግር የምግብ ሉአላዊነት ችግርም አስከተለ ማለት ነው:: ይህ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው:: ምን ይሄ ብቻ፤ ማዳበሪያ ለመግዛት አቅሙ እያላት እንዳይሸጥላት በአቅራቢዎች ላይ ጫና ተደርጎ እንደነበርም ይታወሳል::

ሀገሪቱ በለውጡ መንግሥት ይህን ፈተና ለዘለቄታው ተሻግራዋለች:: በእርዳታ ስንዴ ተጠፍንጋ የኖረችውን ኢትዮጵያ፣ በተለያዩ ጫናዎች ሳቢያ ስንዴ ከዓለም ገበያ እንዳትገዛ ተደርጋ የነበረችው ኢትዮጵያ ፣ ማዳበሪያ መግዣ እንድታጣ ተደርጋ የነበረችው ኢትዮጵያ ከእዚህ ሁሉ እስር ውስጥ ፈልቅቃ ወጥታ በስንዴ ምርት ውጤታማ መሆኗን ዓለም ጭምር የመሰከረላት ለመሆን በቅታለች::

በመኸርና በበልግ ብቻ ይመረት የነበረው፣ ምርታማነቱም እዚህ ግባ ይባል ያልነበረው ስንዴ ፣ በእነዚህ የምርት ወቅቶች በስንዴ የሚሸፈነው ማሳ በእጅጉ እየጨመረ ከመምጣቱም በላይ በሄክታር የሚመረተው ስንዴ መጠንም እየጨመረ መጥቷል::

የስንዴውን ልማት ይበልጥ ከፍታ ላይ ያወጣው ደግሞ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ነው፤ ይህ በቆላማው የሀገሪቱ አካባቢ የተጀመረ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በወይና ደጋና ደጋ አካባቢዎችም እየተስፋፋ ይገኛል:: ከመስኖ ስንዴ ልማት የሚገኘው ምርትም በየዓመቱ እየጨመረ ይገኛል::

በመኸር፣ በበልግና በመስኖ ልማት በየዓመቱ በስንዴ የሚሸፈነው መሬት በእጅጉ እየሰፋ፣ የሚያስገኘው የምርት መጠንም እየጨመረ መጥቷል:: ባለፈው በጀት ዓመት በአጠቃላይ 230 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ የተመረተ ሲሆን፣ ዘንድሮ ደግሞ ይህን አህዝ 300 ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዶ እየተሰራ ነው::

በስንዴ ልማቱ በተገኘው ውጤት ሀገሪቱ ስንዴ ከውጭ ማስመጣት አቁማለች፤ የስንዴ ፍላጎቷን በሀገር ውስጥ ምርት መሸፈን ችላለች:: ከዚህም አልፋ ለጎረቤት ሀገሮች ስንዴ መሸጥ ጀምራለች:: በሰሜኑ ጦርነት ማግስት በተፈጠረ የውጭ ኃይሎች ጫና ለሰብአዊ ድጋፍ የሚያስፈልግ ስንዴ አቅራቢ እንዳይኖር በሀገሪቱ ላይ ዘመቻ በተከፈተበት ወቅት ይህን አቅርቦት የሞላችው ራሷ መሆኗም አቅሟ ምን ያህል እንደጨመረ ከሚያመለክቱት መካከል አንዱ ነው::

ይህን ምርታማነት ለማስቀጠልም በስፋት እየተሰራ ነው:: ይህን ለማድረግ ደግሞ ተፈጥሮም፣ የመንግሥት ዝግጁነትና ቁርጠኝነትም፣ ያለፉት ዓመታት የስንዴ ልማቱ ተሞክሮ ከበቂ በላይ ምቹ ሁኔታዎች ናቸው:: የስንዴ ልማቱ በስንዴ ብቻ ተወስኖ አልቆመም:: ልማቱን በቢራ ገብስ መድገም ተችሏል፤ የቢራ ገብስ ፍላጎት በሀገር ውስጥ ምርት ተሸፍኗል:: ይህን ውጤታማነት በሩዝ፣ በሰሊጥ፣ በለውዝ፣ በአኩሪ አተር፣ በቦሎቄ ልማት ለመድገም እየተሰራ ነው::

እነዚህ ሁሉ የሀገሪቱ ስኬቶች በተለይ በስንዴ ልማት ያስመዘገበችው ታላቅ እምርታ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ተቋማትና ያደጉት ሀገሮች ጭምር መስክረውለታል:: የአፍሪካ ልማት ባንክ መሪዎች የሀገሪቱን የስንዴ ልማት ስኬት ሁሌም ይጠቅሳሉ:: ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ይህንኑ ይናገራሉ::

ሀገሪቱ በቅርቡ ከርሃብ ነጻ የሆነች ዓለም መፍጠርን ያለመው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ማስተናገዷ ይታወቃል፤ ለእዚህ ጉባኤ አዘጋጅነት ስትመረጥ በምክንያት ነው፤ ምክንያቱ ደግሞ የስንዴ ልማቱ ስኬት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል:: በመድረኩም የተለያዩ ወገኖች ይህን ስኬት ጠቅሰውታል:: ቀደም ሲልም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በእዚህ የስንዴ ልማት ባከናወኑት ተግባር የዓለም እርሻ ድርጅት ሽልማት የሰጣቸው መሆኑም ሌላው ታላቅ ምስክርነት ነው::

የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ እንደሚቻል ካለፉት የዘርፉ ስኬቶች ብዙ ተሞክሮዎች ተገኝተዋል:: ግብርናው ሜካናይዝድ እንዲሆን፣ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲያገኝ እየተደረገ ነው፤ በቂ የማዳበሪያ አቅርቦት እንዲኖር ለማድረግ መንግሥት ድጎማ እያደረገ ይገኛል፤ አርሶ አደሩ መሬቱን በባንክ አስይዞ በመበደር ምርትና ምርታማነቱን የሚያሳድግበት ሁኔታም እየተፈጠረ ነው፤ እንደ ማዳበሪያ ያሉ ግብአቶች፣ ባለሙያ፣ ገበያ በሀገር ውስጥም በውጭም ተመቻችቶለታል፤ ዓመታዊ የግብርና ምርትን በእጅጉ ለማሳደግ ታቅዶ እየተሰራም ነው::

የግብርናውን ዘርፍ ስኬቶች ጠቀስኩ እንጂ በኤሌክትሪክ ኃይል ልማት በተለይ በዓባይ ግድብ የተከናወነው ተግባር፣ በኢንዱስትሪው ዘርፍ የማምረት አቅም ከነበረበት እየጨመረ ያለበት ሁኔታ፣ ከውጭ የሚመጡ የኢንዱስትሪ ምርቶችን በመተካት በኩል እየታየ ያለው እምርታ ፣ ሀገሪቱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መዳረሻ እየሆነች ያለችበት ሁኔታ፣ በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት እድገት ከምሥራቅ አፍሪካ ያላት የመሪነት ስፍራ፣ ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገሮች እንዲሁም ከዓለምም የምትገኝባቸው ደረጃዎች ሀገሪቱ ምን ያህል በልማቱ ርቃ እየተጓዘች መሆኗን የሚያመላክቱ ሌሎች ጉልህ ማሳያዎች ናቸው::

እነዚህ ስኬቶች እየተመዘገቡ ባሉበት በእዚህ ዘመን ሀገሪቱ በአንድ ወቅት የነበረችበትን አስከፊ የድርቅ ታሪክ ዛሬም ያለ በሚያስመስል መልኩ መተረክ ውስጥ የገቡ ደካሞች ታይተዋል:: የሀገሪቱን የ1977ቱን ታሪክ እንደ አዲስ በመቀስቀስ የሚወዛወዙ አካላት ከወደ ምእራባውያኑ ብቅ ብለዋል:: ይህ የሀገሪቱን አሁናዊ ለውጥ ዞር ብሎ ያልተመለከተ የቀድሞ ታሪክን በዚህ ወቅት እንደ አዲስ ማቀንቀን ምን ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ መገመት አይከብድም::

በኢትዮጵያ እየሆነ ያለውን እውነታ ለመቀበል ፈቃደኛነቱ የሌላቸው ሆኖ እንጂ ያን ታሪክ አንስተው መቆም አልነበረባቸውም:: አሁን በጥሩ እየተገነባች ለምትገኘው ኢትዮጵያ የበኩላችንን ሚና ተጫውተናል፤ ጠጠር አቀብለናል ቢሉ ይሻላቸው ነበር:: ድጋፉ እዚያ ደረጃ ይደርሳል ከተባለ ማለቴ ነው::

ከዚያ ውጪ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ እነሱም ሆኑ ሌሎች ተመሳሳይ ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት ሲያደርጉ የኖሩትም ሆነ እያደረጉ የሚገኙት አሳ መስጠት እንጂ አሳ እንዴት እንደሚጠመድ ማሳየትን አይደለም፤ ከእነሱ ይልቅ እኛ ድጋፋቸውን እንደ ልማታዊ ሴፍቲኔት ላሉ ተግባሮች እያዋልን የዜጎችን የድርቅ አደጋ ተጠቂነት ለመቀነስ፣ የተጎዱ አካባቢዎች እንዲያገግሙ ለማድረግ ሰርተንበታል::

የድርቅ አደጋ እዚህም እዚያም እየተከሰተ ይገኛል:: ያ አደጋ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ የሚያስችሉ ስራዎች አስቀድሞም አደጋው ከተከሰተ በኋላም በሀገሪቱ ይሰራል:: በዓመታት ጊዜ ውስጥም ያን አስቀያሚ ታሪክ መቀየር የተቻለበት ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፣ ሀገሪቱ በተለይ ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት በተለያዩ ዘርፎች ስኬት በስኬት እየሆነች ትገኛለች::

ሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት ሊነገሩላት ሊተረኩላት የሚገባቸው እነዚህ ስኬቶችና ለስኬቶቹ ያበቋት መንገዶች፣ በእነዚህ ላይ የተመሰረተው ቀጣይ ብሩህ ተስፋዋ እንጂ ያለፉት የክፉ ቀን ታሪኮቿ ብቻ አይደሉም:: እነዚህ በ1970ዎቹ ታሪክ ላይ የቆሙ ወገኖች/ እነዚያ ወገኖች ባለውለታዎቻችን እንደመሆናቸው አሁንም ወገኖች ብንላቸው ችግር የለውም/ ያልተቀየሩ ናቸው:: ያልተቀየረ ወገን ደግሞ የተቀየረውን የኢትዮጵያ እውነታ ሊነግር ሊመሰክር አይችልምና እኛ ለከፍታ ያበቁንን ስራዎቻችንን አጠናክረን እንቀጥላለን!

# ስፖርት





# የስፖርት ማዘውተሪያዎች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ አድርገው እየተገነቡ ነው

ዓስማየሁ ግዛው

በአዲስ አበባ ከተማ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርከት ያሉና የተለያዩ ደረጃ ያላቸው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች እየተገነቡ ይገኛሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ አድርገው በመሰራታቸው ላይ ብዙዎች ጥርጣሬ አላቸው።

ከሰሞኑ ከተማ አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ስፖርት ፌስቲቫል እና ውድድርን ለ14 ጊዜ በማካሄድ ላይ የሚገኘው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ አካል ጉዳተኞችን በስፖርቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የማድረግ ስራ እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጿል። በየደረጃው የሚሰሩ የማዘውተሪያ ስፍራዎች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ እየተገነቡ መሆኑንም ጠቁሟል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የስፖርት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ዳዊት ትርፉ፤ በአሁኑ ወቅት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ አድርጎ መስራት ከመቼውም ጊዜ በላይ ግዴታ መሆኑን ይጠቁማሉ። በከተማዋ የሚገነቡ የስፖርት የማዘውተሪያ ስፍራዎች ከጅምሩም አካል ጉዳተኞችን ከግምት የሚያስገቡ መሆናቸውን የሚያስረዱት ኃላፊው፤ ቀደም ብለው የተገነቡትም ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆኑ በመስተካከል ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል። በዚህም መሰረት የሁሉም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ቀዳሚው መለኪያ ዓይነ ስውራን፣ ዊልቸር ተጠቃሚዎችና እና ሌሎች የጉዳት አይነቶች ያሉባቸውን ያማከሉ መሆኑን ነው የገለፁት። ከዚህ ውጪ ከሆኑም የደረጃ ማረጋገጫና እውቅና ማግኘት አይችሉም። ይህ የክትትልና ቅድመ ሁኔታን



14ኛው የአዲስ አበባ የአካል ጉዳተኞች ስፖርት ፌስቲቫልና ውድድር እየተካሄደ ይገኛል፤

የማሟላት ጉዳይ ትልልቅ ሜዳዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ሌሎች ሜዳዎች ለአካል ጉዳተኞች የማይመቹ ከሆኑ የማስተካከል ስራው እንደሚከናወንም ኃላፊው አስረድተዋል።

በዚህም የስታዲየም መግቢያዎችና መጸዳጃዎችን ጨምሮ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲደረጉ በትኩረት እየተሰራ ነው። ከተማዋም ዘመናዊ ከተማ የምትባለው ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ባማከለ ሁኔታ ስትሰራ እንደሆነ አቶ ዳዊት ያስረዳሉ። ከተማ አስተዳደሩም የአካል ጉዳተኞችን ቁጥር አንዱ አጀንዳው አድርጎ እየሰራ መሆኑን አክለዋል። የሚገነቡት የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎችና መንገዶች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ እያደረጉ በመሆኑም ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች እኩል ትኩረት የመሰጠቱ ማረጋገጫ ነው ይላሉ።

በተጨማሪም በከተማዋ የሚገኙትን አካል ጉዳተኞች ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ ቢሮው ሰፊ ስራዎችን እያከናወነ ሲሆን፣ እነሱን ያማከለና ታሳቢ ያደረገ አደረጃጀቶችም ይገኛሉ። መስማት የተሳናቸው እና የአካል ጉዳተኞች ማህበር ሕዝባዊ አደረጃጀት በአካል ጉዳተኞች ከሚመሩት ውስጥ ይጠቀሳሉ። የውድድር ተሳትፎውን ለማረጋገጥም 11ዱም ክፍለ ከተሞች የውስጥ ውድድሮችን አካሂደው ወደ ከተማ አቀፍ የሚሄዱ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም ተሳትፎን ለማረጋገጥ የተካሄዱት ውድድሮች ምን ዓይነት ፋይዳ እንደነበራቸው ጥናት ተደርጎ ወደዚህ መገባቱም ተጠቁሟል። ከዚህ ቀደም ለመርሃ ግብር ማሟያ ብቻ የሚካሄደው ወድድር አሁን ሁሉም ክፍለ ከተሞች ለአካል ጉዳተኞች ስፖርት በቂ ዝግጅትና ቁሳቁስ እንዲያሟሉ ማድረግ ተችሏል። ከከተማው ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ከመስማት የተሳናቸው፣ ከአካል ጉዳተኞች እና አይነስውራን ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር የረጅም ጊዜ እቅድ ይዞ በመሰራቱም ተሳትፎው እንደጨመረ አቶ ዳዊት አክለዋል።

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፤ በቢሮ በኩል በዓመት አንዴ መሰል ውድድር የሚካሄድ ሲሆን በፌዴሬሽኑ በኩልም የፋይናንስ ድጋፎች በማድረግ ተጨማሪ ውድድሮችን ለማካሄድም ታቅዷል። በቀጣይም የስፖርት ዓይነቶቹን ቁጥርና የጉዳት ዓይነቱን ጨምሮ ለማካሄድ ታቅዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ወይንሸት ግርማ (ዶክተር)፣ ለአካል ጉዳተኞች ስፖርት ትኩረት መሰጠቱንና እነሱን ያማከለ ውድድር እየተካሄደ መሆኑን ይናገራሉ። የአካል ጉዳተኞች ውድድር በከተማ ደረጃ አንዴ ብቻ የሚካሄድ በመሆኑ ሁለት ጊዜ ለማካሄድ ጥረት ይደረጋልም ብለዋል። የአካል ጉዳተኞች አካታችነትና ተጠቃሚነት ላይ የሚታይ ክፍተት በመኖሩ ይህንን ለማረጋገጥ ትኩረት ተሰጥቶና መሬት ላይ ወርዶ መሰራት እንደሚኖርበትም ገልጸዋል።

14ኛው ከተማ አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ስፖርት ፌስቲቫልና ውድድር በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እና የከተማው ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ቢሮ በትብብር ከኅዳር 24/2017 ዓ.ም አንስቶ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ አስተናጋጅነት በድምቀት እየተካሄደ ሲሆን፤ እስከ ታህሳስ 6/2017 ዓ.ም በፉክክሮች ታጅቦ ይቀጥላል። ውድድሩ “የአካል ጉዳተኞችን የመሪነት ሚና በማጉላት አካታችነትን እና ዘላቂ ልማትን እናረጋግጥ” በሚል መሪ ቃል በአትሌቲክስ፣ በዳርት፣ በጠረጴዛ ቴኒስ፣ ክብደት ማንሳትን ጨምሮ በ7 የስፖርት ዓይነቶች ከ10 ሺ በላይ አካል ጉዳተኛ ስፖርተኞች ይሳተፉበታል።